የኢየሱስ ክርስቶስ

# ምሳሌዎች ።



፫ኛ መጽሐፍ

$0.75

@et_christian_library

# የኢየሱስ ክርስቶስ

# ምሳሌዎች ።

የኢየሱስ ታሪክ

የተባለው መጽሐፍ ተከታይ ።

ከብርሃን ሕይወት መጻሕፍት ።

በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት

ዘኢትዮጵያ በሠላሳ ሰባተኛው ዘመን መንግሥት ።

አዲስ አበባ ፲፱፻፶፱ ዓ. ም.

በሴንትራል ማተሚያ ቤት ታተመ ።

@et_christian_library

Published in cooperation with
**The Committee on World Literacy**
**and Christian Literature**
1963 Edition

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙት ጥቅሶች በ፲፱፻፶፫ ዓ. ም. በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መልካም ፈቃድና ትእዛዝ እማርኛው ታርሞ ከታተመው መጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሱ ናቸው ።

Illustrations by courtesy of
David C. Cook Publishing Company
Elgin, Illinois, U.S.A.

@et_christian_library

# ማውጫ


| | | ገጽ |
|---|---|---|
| | መቅድም | 3 |
| ፩ ፤ | የዘሪው ምሳሌ ። | 5 |
| ፪ ፤ | የእንክርዳዱ ፡ ምሳሌ ። | 7 |
| ፫ ፤ | የሰናፍጭ ቅንጣት ምሳሌ ። | 9 |
| ፬ ፤ | ዋጋዋ ፡ እጅግ የበዛ ዕንቍ ። | 11 |
| ፭ ፤ | መንግሥተ ፡ ሰማያት መረብን ትመስላለች ። | 13 |
| ፮ ፤ | መንግሥተ ፡ ሰማያት ባለቤትን ትመስላለች ። | 15 |
| ፯ ፤ | መንግሥተ ሰማያት የሚገቡ እነማን ናቸው ? | 17 |
| ፰ ፤ | የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ስለ ምን እንዳልጦሙ ። | 19 |
| ፱ ፤ | አዲሱና አሮጌው ። | 21 |
| ፲ ፤ | ሠራተኞች በወይን አትክልት ውስጥ እንደ ሠሩ ። | 23 |
| ፲፩ ፤ | የታማኙና የሃኬተኛው አገልጋይ ምሳሌ ። | 25 |
| ፲፪ ፤ | የዓመፀኛው መጋቢ ምሳሌ ። | 27 |
| ፲፫ ፤ | ክፉው አገልጋይ ። | 29 |
| ፲፬ ፤ | ባለ ጠጋው ሰውና አልዓዛር ። | 31 |
| ፲፭ ፤ | ሰነፉ ባለ ጠጋ ሰው ። | 33 |
| ፲፮ ፤ | መልካሙ ባልንጀራ ። | 35 |
| ፲፯ ፤ | የግብዣው ምሳሌ ። | 37 |
| ፲፰ ፤ | ዳግመኛ መወለድ ። | 39 |
| ፲፱ ፤ | አሥር ቈነጃጅት በሰርግ ። | 41 |
| ፳ ፤ | የመጨረሻው ፡ ፍርድ ። | 43 |
| ፳፩ ፤ | ስለ ብፁዓን ። | 45 |
| ፳፪ ፤ | በፍጥነት ታረቁ ። | 48 |
| ፳፫ ፤ | ጠላቶቻችሁን ውደዱ ። | 50 |
| ፳፬ ፤ | የጌታችን ጸሎት ። | 52 |
| ፳፭ ፤ | አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ፈልጉ ። | 54 |

# መቅድም

ይህ የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌዎች የተባለው መጽሐፍ ፣ ስለ ኢየሱስ ታሪክ ከሚናገሩት ሦስት ተከታታይ የንባብ መልመጃ ጽሑፎች ሦስተኛው ነው ። የተዘጋጀውም ፣ የንባብ መልመጃ ጽሑፎቻቸውንና ፡ ከኢየሱስ ታሪክ አንደኛውንና ሁለተኛውን መጻሕፍት ፣ ማለት የኢየሱስ ልደትና አገልግሎት ፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ የተባሉትን ፣ ላጠናቀቁ ጀማሪ አንባቢ ዎች ነው ።

የዚህ መጽሐፍ ዓላማ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገራቸውን ምሳሌ ዎች ቀለል ባለ መንገድ መግለጥ ሲሆን ፣ በተጨማሪም ፣ አንባቢው አራ ቱን ወንጌሎች ራሱ እንዲያነብ ማዘጋጀት ነው ። አንባቢው ትምህርቱን በሚከታተልበት ጊዜ ከወንጌል ጋር ያስተያይ ዘንድ ፣ በየምዕራፉ መጨረሻ ትምህርቱ የሚገኝበት ክፍል ተገልጦአል ።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡትን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች ለመምረ ጥና ለማዘጋጀት መሪ አድርጌ የተጠቀምኩበትን መጽሐፍ የደረሱትን ዶክ ተር ፍራንክ ሲ. ላውባክን አመሰግናለሁ ።

አልበርት ሲ. አስትሮንግ ።

@et_christian_library

፩

# የዘሪው ምሳሌ ።



@et_christian_library

ኢየሱስ ብዙ ምሳሌዎች ተናገረ ። እነዚህን ምሳሌዎች ለደቀ መዛሙርቱና በዙሪያው ለተሰበሰቡት ሰዎች ነገራቸው ። የነገራቸውም ምሳሌዎች ሁሉ አጫጭሮች ናቸው ። ይህ መጽሐፍ ፤ ኢየሱስ ከተናገራቸው ምሳሌዎች አንዳንዶቹን ይዞአል ።

ይህ የመጀመሪያው ምሳሌ ዘርን ሊዘራ ስለ ወጣ ገበሬ ነው ። ገበሬው አንድ ከረጢት ሙሉ ዘር ይዞ ሊዘራ ወጣ ። ነገር ግን የዘራው ዘር ሁሉ በታረሰው መሬት ላይ አልወደቀም ። አንዳንዱ በመንገድ ዳር ወደቀ ። በመንገዱም ዳር የነበረው መሬት ያልታረሰ ነበርና ዘሩ እመሬቱ ውስጥ ሊገባ አልቻለም ። በዚያም አጠገብ ብዙ ወፎች ስለ ነበሩ ፤ በመንገዱ ዳር የወደቀውን ዘር በሉ ። ወፎቹ ዘሩን ስለ በሉት ፤ በመንገዱ ዳር ከወደቀው ዘር አንድ እንኳ አልበቀለም ።

በታረሰው መሬት ውስጥ አልፎ አልፎ ጭንጫ ነበረ ። ገበሬው የዘራው አንዳንዱ ዘር በዚሁ ብዙ አፈር በሌለበት ጭንጫ ላይ ወደቀ ። ብዙ አፈርም ስላልነበረው ፤ ወዲያው በቀለ ። ቡቃያም ሆነ ። ፀሐይ በወጣ ጊዜ ግን ጠወለገ ፤ ሥርም ስላልነበረው ደረቀ ። አድጎ ትልልቅ ለመሆን አልቻለም ።

ከመሬቱ ጥቂቱ ደግሞ አረምና እሾህ ነበረበት ። ገበሬው የዘራው አንዳንዱ ዘር በእሾሁ መካከል ወደቀ ። ዘሩም በቶሎ በቀለ ። ነገር ግን እሾሁ አብሮት በቀለ ። ከአትክልቱም ፈጥኖ አደገ ። ስለዚህ አትክልቱን አነቀው ። ገደለውም ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ እሾሁ ብቻ ቀረ ። በእሾሁ መካከል ከነበረው አትክልት እጥፍ ፍሬ ለማፍራት አንድ እንኳ አላደገም ።



@et_christian_library

ከመሬቱ ጥቂቱ ግን መልካም ነበረ ። ገበሬው የዘራው አንዳንዱ ዘር በዚህ በመልካም መሬት ላይ ወደቀ ። በቅሎም አደገ ። አንዱ ሠላሳ እጥፍ ፥ አንዱም ስልሳ እጥፍ ሌላውም መቶ እጥፍ አፈራ ።

ደቀ መዛሙርቱ ፦ ይህ ምሳሌ ምንድር ነው ? ብለው ኢየሱስን ጠየቁት ። ስለዚህ ኢየሱስ እንዲህ ብሎ ገለጠላቸው ፦ እግዚአብሔር በሰው ልብ ውስጥ መልካም ዘር ይዘራል ። ዘሩ የእግዚአብሔር ቃል ነው ። መሬቱም የሰው ልብ ነው ። አንዳንድ ሰዎች በመንገድ ዳር እንዳለው መሬት ናቸው ። የእግዚአብሔርን ቃል ይሰማሉ ። ዳሩ ግን ዘሩን እንደ በሉት ወፎች ዲያብሎስ ይመጣና ቃሉን ከልባቸው ይወስዳል ። ይህንም ያደረገበት ምክንያት ፥ ሰዎች አምነው እንዳይድኑ ነው ። አንዳንድ ሰዎች ደግሞ እንደ ጭንጫው መሬት ናቸው ። የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው በደስታ ይቀበሉታል ። ቃሉ በልባቸው ውስጥ ለአጭር ጊዜ ይቆያል ። ነገር ግን በቃሉ ምክንያት ትንሽ መከራ ወይም ስደት ሲደርስባቸው ፥ እምነታቸውን ይጥላሉ ። ሌሎች ሰዎች ደግሞ እሾህ እንዳለበት መሬት ናቸው ። የእግዚአብሔር ቃል በልባቸው ተዘርቶአል ። ዳሩ ግን እነዚህ ሰዎች በብዙ ዓለማዊ ነገሮች የታነቁ ስለ ሆኑ ፥ የእግዚአብሔርን ቃል ለመመልከት ጊዜ ያጡ ናቸው ። የዚህ ዓለም አሳብና የባለጠግነት ምኞት ቃሉን ያንቃል ። ሕይወታቸውም የማያፈራ ይሆናል ።

ነገር ግን አንዳንድ ሰዎች እንደ መልካሙ መሬት ናቸው ። የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው ያስተውላሉ ። በልባቸው ያኖሩታል ። እርሱም ያድግና ብዙ ፍሬ ያፈራል ።

(ሉቃ. ፰ ፥ ፬—፲፭ ፤ ማቴ. ፲፫ ፥ ፲፰—፳፫ ተመልከት ።)



## ፱

## የእንክርዳዱ ምሳሌ ።

ኢየሱስ ስለ ግብርና ያውቅ ነበር ። በግብርና አልኖረም እንጂ ባደገበት ከተማ በናዝሬት አካባቢ ብዙ እርሻዎች ነበሩ ። እርሱም ብዙ ጊዜ በእነዚህ እርሻዎች ውስጥ እየሄደ ፡ ገበሬዎቹ ሲሠሩ ይመለከት ነበር ።

አንደኛው ምሳሌ ስለ መልካም መሬትና ስለማያፈራ መሬት ነበረ ። የሚቀጥለው ምሳሌ ስለ መልካም ዘርና ስለ መጥፎ ዘር ነው ። ሰብልን መልካም ከሚያደርጉ ነገሮች አንዱ ፣ መልካም ዘር ነው ። ሰብልን መልካም ከሚያደርጉት ነገሮች ሌላው ፣ መልካም መሬት ነው ። መሬቱ መልካም ነው ወይስ መጥፎ ? መሬቱ መጥፎ ከሆነ ፡ እንዲሁም ሰብሉ መጥፎ ይሆናል ። ስለዚህ ሰብሉ በብዙዎቹ ነገሮች መልካምነት ላይ የተደገፈ ነው ። ሰብልን መልካም የሚያደርገው ሌላው ነገር ደግሞ ውኃ ነው ። በቂ ውኃ ከሌለ ፡ ሰብሉ የማያፈራ ይሆናል ። በተለይም ሰብሉን መልካም የሚያደርገው ነገር ፡ የተዘራው ዘር ዓይነት ነው ። አንድ ዓይነት ዘር ብትዘራ ፡ ሰብሉም ልክ እንደ ተዘራው ዘር ዓይነት ይሆናል ። መልካም ዘር ብትዘራ ፡ ሰብሉም መልካም ይሆናል ። መጥፎ ዘር ብትዘራ ፡ ሰብሉም መጥፎ ይሆናል ።

ሰብሉ መልካም እንዲሆን የሚያስፈልገው አንድ ሌላ ነገር ደግሞ አለ። እርሱም የፀሐይ ብርሃን ነው ። በቂ ፀሐይ ያስፈልገዋል ። ዳሩ ግን ፀሐይዋ በጣም ኃይለኛ ከሆነች ፡ ሰብሉን ታጠወልገዋለች ። ፀሐይዋ ደግሞ የሚያስፈልገውን ያህል ብሩህ ካልሆነች ፡ ሰብሉ በጭራሽ አያድግም ።

ኢየሱስ እንዲህ አለ ፦ አንድ ቀን አንድ ገበሬ በእርሻው ውስጥ ዘር ለመዝራት ፈለገ ። ከዘር ዓይነት ሁሉ መልካሙን ገዝቶ ቢዘራ ፡ ከሁሉ ገበሬዎች የተሻለ ሰብል እንደሚያገኝ አመነ ። ስለዚህ ሊያገኝ ከሚችለው ዘር ሁሉ መልካሙን ገዛ ።

ያንን መልካም ዘር ከገዛ በኋላ ፥ በእርሻው ዘራው ።

ነገር ግን ማታ ተኝቶ ሳለ ፥ ጠላቱ መጣና በእርሻው መጥፎ ዓይነት ዘር ዘራ ። ይህም ዘር እንክርዳድ ነበረ ።

መልካሙም ዘር በቀለና ቡቃያ ሲሆን ፥ እንክርዳዱ ደግሞ ይታይጀመር ። ሠራተኞቹም ፦

ጌታ ሆይ ፥ መልካምን ዘር በእርሻህ ዘርተህ አልነበርህምን ? እንክርዳዱንስ ከወዴት አገኘ ? አሉት ።

ገበሬውም ፦ ጠላት ይህን አደረገ አላቸው ።

ሠራተኞቹም ፦ እንክርዳዱን እንልቀመውን ? ሲሉ ጠየቁት ።

ገበሬውም እንዲህ አላቸው ፦ እንክርዳዱን ስትለቅሙ ምናልባት እህሉን ከእርሱ ጋር እንዳትነቅሉት አይሆንም ። ተዉአቸው ፤ እስከ መከር ጊዜ አብረው ይደጉ ። በመከር ጊዜም አጫጆችን ጠርቼ ፦ እንክርዳዱን አስቀድማችሁ ልቀሙ ፤ በእሳትም ለማቃጠል በየነዶው እሰሩ ፤ እህሉን ግን በጎተራዬ አከማቹ አላለሁ ።

ደቀ መዛሙርቱ ይህን ከሰሙ በኋላ ፦ ይህ ምሳሌ ምንድር ነው? ብለው ኢየሱስን ጠየቁት ። ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው ፦ መልካምን ዘር የዘራው የሰው ልጅ ነው ፤ እርሻውም ዓለም ነው ፤ መልካሙም ዘር የመንግሥት ልጆች ናቸው ፤ እንክርዳዱም የክፉው ልጆች ናቸው ፥ የዘራውም ጠላት ዲያብሎስ ነው ፤ መከሩም የዓለም መጨረሻ ነው ፥ አጫጆችም መላእክት ናቸው ። እንግዲህ እንክርዳድ ተለቅሞ በእሳት እንደሚቃጠል ፥ በዓለም መጨረሻ እንዲሁ ይሆናል ። የሰው ልጅ መላእክቱን ይልካል ፥ ከመንግሥቱም እንቅፋትን ሁሉ ዓመፃንም የሚያደርጉትን ይለቅማሉ ፥ ወደ እሳትም ይጥሉአቸዋል ። ነገር ግን እህሉ በጎተራ እንደሚከማች ፥ ጻድቃን በአባታቸው በእግዚአብሔር መንግሥት ይሰበሰባሉ ።

(ማቴ. ፲፫ ፥ ፳፬—፴ ፤ ፴፮—፵፫ ተመልከት ።)




# ፫

# የሰናፍጭ ቅንጣት ምሳሌ ።

@et_christian_library

አንድ ቀን ኢየሱስ ፦ መንግሥተ ሰማያት ሰው ወስዶ በእርሻው የዘራትን የሰናፍጭ ቅንጣት ትመስላለች አለ ።

የሰናፍጭ ቅንጣት መጠንዋ ትንሽ ነው ። በመጠን እንደ ሰናፍጭ ቅንጣት ያነሰ ዘር ለማግኘት አስቸጋሪ ነው ። ባደገች ጊዜ ግን ፣ ከአትክልቶች ሁሉ ትበልጣለች ።

አንድ ገበሬ የሰናፍጭ ቅንጣት ዘራ ። እርሰዋም በቶሎ በቀለች ። ከጥቂት ወራት በኋላ መጠንዋ እንደ አንድ ትንሽ ዛፍ ሆነ ። ይህን ያህል ካደገች በኋላ ፣ ወፎች መጡና ቤታቸውን ሠርተው አረፉባት ።

ኢየሱስ መንግሥተ ሰማያትን በሰናፍጭ ቅንጣት የመሰለው ለምንድር ነው ? የመሰለበት ምክንያት ፣ መንግሥተ ሰማያት በመጀመሪያ ትንሽ ሰለ ነበረች ነው ። ኢየሱስ ሰለ እግዚአብሔር መንግሥት መስበክ በጀመረ ጊዜ ፣ ቃሉን የተቀበሉት ጥቂቶች ነበሩ ። የእግዚአብሔር ግዛት በሰዎች መካከል እንደ ሰናፍጭ ቅንጣት መሰለች ። ነገር ግን የዓለም መንግሥት የእርሱ እስከትሆን ድረስ እግዚአብሔር መንግሥቱን እንደሚያስፋፋ ፣ ኢየሱስ ያውቅ ነበር ። ስለዚህ የሰማይ ወፎች መጥተው በቅርንጫፎችዋ እስኪሰፍሩ ድረስ እንደምታድግ የሰናፍጭ ቅንጣት የእግዚአብሔር መንግሥትም እንደ ምታድግ አስተማረ ።



@et_christian_library

ኢየሱስ መንግሥተ ሰማያትን በሰናፍጭ ቅንጣት የመሰለበት ሌላው ምክንያት ደግሞ ፣ ሁለቱም ሕይወት ስላላቸው ነው ። ሁለቱም ሕይወት ስላ ላቸው ያድጋሉ ። እግዚአብሔር ለሰናፍጭ ቅንጣት ሕይወት ስለሚሰጣት ፣ እያደገች ትሄዳለች ። ለመንግሥተ ሰማያት ወራሾችም ሕይወትን የሚሰጥ እርሱ ነው ። እግዚአብሔር ለመንግሥተ ሰማያት ወራሾች ሕይወትን ስለሚሰጣቸው ፣ መንግሥቱ እየሰፋች ትሄዳለች ።

ኢየሱስ ስለ አንድ ሌላ ዘሪ ደግሞ በጣም አጭር የሆነ ምሳሌ ተናገረ። ይህ ገበሬ ዘርን በእርሻው ዘራ ። ከጥቂት ቀናት በኋላ ቡቃያው ከመሬት ብቅ ሲል አየ ። ከጥቂት ወራት በኋላ ደግሞ ለመታጨድ ዝግጁ መሆኑን ተረዳ ። ገበሬው ተኝቶ ሳለ ፣ እግዚአብሔር ዘሩን አብቅሎ አሳደገው ። ገበሬው ሳያውቅ ፣ ቀንና ሌሊት ዘሩ እያደገ ሄደ ።

ኢየሱስ ይህን በእግዚአብሔር መንግሥት መሰለው ። ገበሬው ዘሩን ሊያ በቅል ይቅርና እንዴት በቅሎ እንዳደገ እንኳ አላወቀም ። እግዚአብሔር ዘሩን ያበቀለው በማይመረመር ምሥጢሩ ነውና ። የእግዚአብሔር መንግሥ ትም እንዲሁ ነው ። እኛ በራሳችን ችሎታ ልናስፋፋው አንችልም ። በማይመ ረመር ምሥጢሩ የሚያሳድገው እግዚአብሔር ብቻ ነው ። እኛ የሚቻለን የእርሱን መንግሥት ከነምሥጢሩ በእምነት መቀበል ብቻ ነው ።

ገበሬው ዘሩን በአንድ ጊዜ በቅሎ ሲያድግ አላየም ። ነገር ግን ማታና ቀን ሲተኛም ሲነሣም ፣ ቀስ በቀስ ያድግ ነበር ። ከብዙ ጊዜ በኋላ ግን እንዳደገ ለማየት ቻለ ። ደግሞ አንድ ቀን መከር ደረሰ ። በዚያን ጊዜ ሰብሉ ተሰበሰበ አረሙም ተጣለ ። የእግዚአብሔር መንግሥትም እንዲሁ ነው ። እግዚአብሔር ቀስ በቀስ መንግሥቱን ያሳድጋል ። ግን ማደጉን ሁልጊዜ ልናይ አንችልም ። የሆነ ሆኖ ፣ ያለ ትዕግሥት መኖር የለብንም ። የእግዚአብ ሔር ፈቃድ በሰማይ እንደ ሆነ እንዲሁ በምድር የሚሆንበትን ቀን በተ ስፋ እየጠበቅን መኖር አለብን ። ደግሞ የእግዚአብሔር መንግሥት ለሚፈ ጸምበት ቀን ተዘጋጅተን እየጠበቅን እግዚአብሔርን ለማየት እንናፍቅ ።

(ማቴ. ፲፫ ፣ ፴፩ ፣ ፴፪ ፤ ማር. ፬ ፣ ፳፮—፳፱ ተመልከት ።)



፬

ዋጋዋ እጅግ የበዛ
ዕንቍ ።

ኢየሱስ ሰዎች በቀላሉ እንዲረዱ በማለት ፣ በምሳሌዎች አስተማረ ። ሕዝቡ ዘወትር በሚያዩአቸውና በሚጠቀሙባቸው ነገሮች ተጠቀመ ። እነዚህን ነገሮች የተጠቀመባቸው ፣ የመንግሥት ሰማያትን ጥልቅ ምሥጢርና የመንፈስን ነገሮች ለመግለጥ ነበረ ። ጥልቅ የሆነ ምሥጢርን ለመግለጥ ከሚያገለግሉ ዘዴዎች አንዱ ፣ ምሥጢሩን ሰዎች በሚያውቁት ነገር መመስል ነው ። ኢየሱስ በገበሬውና በዘሩ ምሳሌ የተጠቀመው ፣ ሕዝቡ ገበሬና ዘር ምን እንደ ሆኑ በደንብ ያውቁ ስለ ነበረ ነው ። በሚያውቁት ነገር አማካይነት ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ጥልቁን ምሥጢር ሊያስተውሉ ይችሉ ነበር ። ኢየሱስ በምሳሌ በብዙ ያስተማረው ስለዚህ ነው ።

ኢየሱስ በዚህ ምድር በኖረበት ዘመን ፣ ዕንቍ በቅድስት አገር በጣም የታወቀ ነበር ። አብዛኞቹም ዕንቍን አይተዋል ። ከፍ ያለ ዋጋ እንደሚያወጣም ያውቁ ነበር ። ስለዚህ ኢየሱስ ስለ መንግሥተ ሰማያት ጥልቁን ምሥጢር ለመግለጥ ፣ ስለ አንዲት ዕንቍ ይህን ምሳሌ ተናገረ ፤—

አንድ ነጋዴ መልካምን ዕንቍዎችን ሲሻ ፣ ዋጋዋ እጅግ የበዛ አንዲት ዕንቍ አገኘ ። ነጋዴውም እንዲህ አለ ፣—

ይህች ዋጋዋ እጅግ የበዛ ዕንቍ ናት ። በቤቴ ያለው ነገር ተሰብስቦ ቢሸጥም ፣ የዕንቍዋን ዋጋ አይከፍልም ። ከሌሎቹ ከተሰበሰቡት ዕንቍዎቼ ዋጋ በላይ ይጠይቃል ። ይህችን ዋጋዋ እጅግ የበዛ አንዲት ዕንቍ እንድገዛ፣ በቤቴ ያሉኝን ነገሮችና ሌሎቹንም ዕንቍዎቼን ሁሉ እሸጣለሁ ።

ስለዚህ ነጋዴው ባለ ዕንቍዋን ፦— ይህችን ዕንቍ መግዛት እፈልጋለሁ። ዋጋዋ ስንት ነው ? አለው ።

ባለ ዕንቊዋም የዕንቊዋን ዋጋ ነገረው ።

ስለዚህ ነጋዴው ቤቱን ሸጠ ። ሌሎች ዕንቊዎቹን ሸጠ ። የነበረውን ነገር ሁሉ ሸጠ ። ትልቅዋንና መልካምዋን ዕንቊ ለመግዛት በቂ ገንዘብ እንዲያገኝ ፣ ያለውን ነገር ሁሉ ሸጠ ።

በኋላም ዕንቊዋን ለመግዛት ሄደ ። አሁን ዕንቊዋን ለመግዛት በቂ ገንዘብ አለኝ አለ ። ስለዚህ ባለ ዕንቊዋ ዕንቊዋን ሸጠለት ። ነጋዴውም ዕንቊዋን ባገኘ ጊዜ ፣ በጣም ተደሰተ ።

ይህ መንግሥተ ሰማያትን ለመግለጥ ጥሩ ምሳሌ ነበረ ። ምክንያቱም ፣ በዚያን ጊዜ ነጋዴዎች ዕንቊዎች ሲገዙና ሲሸጡ ፣ ሁሉም አይቶአል ። ደግሞም ትልልቆቹ ዕንቊዎች ምን ያህል እንደሚያወጡ ያውቁ ነበር ። ስለዚህ ኢየሱስ ለመንግሥተ ሰማያት ምን ያህል ግምት እንደሚሰጠው ሁሉም አስተዋሉ ።

ኢየሱስ መንግሥተ ሰማያት ይህን ነጋዴ ትመስላለች ያለው ሰምን ድር ነው ? እኛ ወደ መንግሥተ ሰማያት ለመግባት ያን ያህል ገንዘብ ይፈለ ግብናል ማለቱ ነውን ? ወይስ እኛ መንግሥተ ሰማያት ለመግባት ያለንን ሁሉ መሸጥ ይገባናል ማለቱ ነው ? ወይስ እኛ በሕይወታችን የእግዚአብሔ ርን መንግሥት ከሁሉ አብልጠን መሻት አለብን ማለቱ ነው ? አንድ ጊዜ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ፦— አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ፈልጉ ። - - - ስለ እኔና ስለ ወንጌል - - - ሁሉንም የተወ ፣ አሁን በዚህ ዘመን ከስደት ጋር - - - መቶ እጥፍ ፣ በሚመጣውም ዓለም የዘላለም ሕይወት የማይ ቀበል ማንም የለም አለ ።

(ማቴ. ፲፫ ፣ ፵፭ ፡ ፵፮ ተመልከት ።)



፫

መንግሥተ ሰማያት
መረብን ትመስላለች ።

@et_christian_library

የገሊላ ባሕር ኢየሱስ ከኖረበት ሰፍራ ሩቅ አልነበረም ። በልጅነቱ ጊዜ ዓሣ አጥማጆች ዓሣ ሲያጠምዱ ፣ ብዙ ጊዜ ይመለከት ነበር ። ስለዚህ ከአጫጭር ምሳሌዎቹ በአንዱ ፣ መንግሥተ ሰማያትን እንዲህ ሲል በመረብ መሰላት ፡—

ደግሞ መንግሥተ ሰማያት ወደ ባሕር የተጣለች መረብን ትመስላ ለች ። ይህችም መረብ ከሁሉም ዓይነት ዓሣ ሰበሰበች ። በሞላችም ጊዜ አጥ ማጆች ወደ ወደቡ አወጡአትና ብዙ ዓይነት ዓሣ እንደ ሰበሰቡ ተመለከቱ። ከዓሣው አብዛኛው ለመብል መልካም ሲሆን ፣ ጥቂቱ ግን ለመብል መጥፎ ፣ መሆኑን አዩ ። ስለዚህ መልካሙን ዓሣ ከመጥፎው ዓሣ ለዩና መጥፎውን ወደ ውጭ ጣሉ ። መልካሙን ዓሣ ግን በቅርጫቶች ውስጥ አከማቹና ቅርጫ ቶቹን ተሸከመው ወደ ቤታቸው ወሰዱ ። በዚያን ቀን አብዛኞቹ ሰዎች ዓሣ በሉ ።

ይህ ምሳሌ በገሊላ ባሕር ዳር ይኖሩ ለነበሩት ሰዎች ለመንገር ጥሩ ምሳሌ ነበረ ። በባሕሩ ዳር ይኖሩ የነበሩት ሰዎች ሁሉ ዓሣ አጥምደዋል ፤ ወይም ሌሎች ሰዎች ሲያጠምዱ አይተዋል ። ደግሞም በባሕሩ ዳር ይኖሩ የነበሩ ሰዎች ሁሉ ቅርጫቶች ነበሩአቸው ። ቅርጫቶቹን ዓሣ ለመያዝ ይጠቀሙባቸው ነበር ። በባሕሩ ዳር ይኖሩ የነበሩ ሰዎች ሁሉ ፣ መልካሙ ዓሣ ከመጥፎው ሲለይ አይተዋል ። ከደቀ መዛሙርቱ አያሌዎቹ በባሕር ዳር ይኖሩ ስለ ነበር ፣ ዓሣ እያጠመዱ ኖረዋል ።

ስለዚህ ኢየሱስ መንግሥተ ሰማያት ከሁሉም ዓይነት ዓሣ የሰበሰበች መረብን ትመስላለች የሚለውን ምሳሌ ተጠቀመበት ። መረብ መንግሥተ

ሰማያትን የሚመስለው በምን ነው ? በአያሌ መንገዶች ይመስላል ። አንዱ መንገድ ይህ ነው ፡— በመንግሥተ ሰማያት ኃጢአተኞችን ከጻድቃን መካከል ይለዩአቸዋል ። ኢየሱስ ፡— ይህ በዓለም መጨረሻ ይሆናል ፤ መላእክት መጥተው ኃጢአተኞችን ከጻድቃን መካከል ይለዩአቸዋል ፡ ወደ እቶን እሳትም ይጥሉአቸዋል ፤ በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል አለ ።

ይህ ምሳሌ የተነገረበት ምክንያት ምንድር ነው ? ኢየሱስ ኃጢአተኞች ከጻድቃን እንደሚለዩ የሚነግረን በዚህ መንገድ ነው ። ኃጢአተኞች ሁሉ የሚጠፉት በዚህ አኳኋን ነው ። ጻድቃን ወደ መንግሥተ ሰማያት ይገባሉ ። ሌሎች ግን ሊገቡ አይችሉም ።

ኢየሱስ ይህ በዓለም መጨረሻ ይሆናል አለ ። በአሁኑ ዘመን ዓለም በክፋት ተሞልታለች ። በዚህ በአሁኑ ዘመን እግዚአብሔር ኃጢአታችሁን ተናዘዙ ይለናል ። በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የኃጢአታችንን ይቅርታ እንድናገኝና ልጆቹ እንድንሆን ይፈልጋል ። በዚህ በአሁኑ ዘመን ብዙ ክፋት ቢኖርም ፡ በንቃትና በቅንነት እንድንኖር ይፈልጋል ። ኃጢአተኞች ከጻድቃን ለሚለዩበት ለዓለም መጨረሻ እንድንዘጋጅ ይፈልጋል ። ከኃጢአተኞች ጋር እንድንቃጠል አይፈልግም ።

የዘመኑ መጨረሻ መቼ ይሆናል ? ደቀ መዛሙርቱ አላወቁም ። ቀኑ መቼ እንደሚሆንም የሚያውቅ ሰው የለም ። ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስን ፡— የዓለም መጨረሻ መቼ ነው ? ሲሉ ጠየቁት ። ኢየሱስም እንዲህ ብሎ መለሰላቸው ፡—

እናንተ ይህን ለማወቅ አልተሰጣችሁም ። የዓለም መጨረሻ መቼ እንደሚሆን ማንም አያውቅም ። ስለዚያች ቀን ወይም ሰዓት የሰማይም መላእክትም ቢሆኑ ልጅም ቢሆን ከአባት በቀር የሚያውቅ የለም ።

ስለዚህ የዓለም መጨረሻ መቼ እንደሚሆን አውቃለሁ የሚለን ሰው ቢኖር ፡ አለማወቁን ያግሞም ይህን ከእግዚአብሔር በቀር የሚያውቅ አለመኖሩን ልንነግረው እንችላለን ። እግዚአብሔር ይህን ያደረገበት ፡ የራሱ ምክንያት አለው ።

(ማቴ. ፲፫ ፡ ፵፯—፶ ፤ ማር. ፲፫ ፡ ፴፪—፴፫ ተመልከት ።)

# ፮

# መንግሥተ ሰማያት ባለቤትን ትመስላለች ።

አንድ እጅግ በጣም አጭር የሆነ ምሳሌ አለ ። ይህ ምሳሌ አንድ ዓረ ፍተ ነገር ብቻ ነው ። ዓረፍተ ነገሩም ይኸው ፦—

ስለዚህ የመንግሥተ ሰማያት ደቀ መዝሙር የሆነ ጸሐፊ ሁሉ ከመዝ ገቡ አዲሱንና አሮጌውን የሚያወጣ ባለቤትን ይመስላል ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደሚገኙት እንደ ብዙዎቹ ሌሎች ዓረፍተ ነገሮች ፥ ይህ ምሳሌም በእርግጥ በጣም ጥልቅ ትርጉም አለው ። ምክንያቱም፥ መጽሐፍ ቅዱስ ጥልቅ ምሥጢራት የሚገኙበት መጽሐፍ ስለ ሆነ ነው ። ዓረፍተ ነገሩ በጣም አጭር ቢሆን እንኳ ፥ አብዛኛውን ጊዜ ትርጉሙ በጣም ጥልቅ ነው ።

አሁን የዚህን የአንድ ዓረፍተ ነገር ምሳሌ ጥልቅ ትርጉም እንማራለን። በመጀመሪያ መማር የሚገባን ፥ ጸሐፊ የሚለውን ቃል ትርጉም ነው ። ኢየ ሱስ ክርስቶስ በዚህ ምድር በተመላለሰበት ዘመን ፥ ጸሐፊ የሚለው ቃል ሁለት ትርጉሞች ነበሩት ። አንደኛው ትርጉም ሕግን በመጻፍ የሠለጠነ ሰው ማለት ነበረ ። በዚያን ጊዜ ሕግ በበቂ ግልባጭ እንዲገኝ ፥ ሕግን የሚገለብጥ ሰው መሠልጠን ነበረበት ። ጌታችን በምድር በተመላለሰበት ዘመን የማተ ሚያ መኪናዎች አልነበሩም ። ዛሬ ሰው መጽሐፍ ሲጽፍ ፥ አንድ ጊዜ ብቻ ይጽፍና የማተሚያ መኪናዎች ያባዙታል ። ስለዚህ ማተሚያ መኪናዎች ባል ነበሩአቸው ጊዜ ፥ እየደጋገሙ በእጅ መጻፍ ነበረባቸው ።

የመጀመሪያው ማተሚያ መኪና የተሠራው ከክ. ልደት በኋላ በ፲፬፻ ፶፬ ዓመት ነው ። የማተሚያ መኪና ከመሠራቱ በፊት ፥ ጸሐፊዎች መጻሕፍ ትን በእጅ ጽሕፈት መገልበጥ ነበረባቸው ። ይህንም ጥሩ አድርጎ ለመሥ ራት ብዙ ዓመታት መሠልጠን ነበረባቸው ። ለዚህ ሥራ የሚሠለጥነውም ሰው ደንበኛ አጻጻፍ እንዲያውቅ ይሠለጥን ነበር ። ጸሐፊ እንደ ትልቅ ሰው ይገመት የነበረው ስለዚህ ነው ።

የጸሐፊ ሁለተኛው ትርጉም ሕግን ለማስተማር የሠለጠነ ሰው ማለት ነበረ ። ይህ ሰው ጸሐፊም መምህርም ነበረ ። ሕግን ብዙ ጊዜ እየደጋገመ ስለ ሚጽፍና ሕጉን ሁሉ በቃሉ ያውቀው ስለ ነበር ፥ ጥሩ የሕግ አስተማሪ ነበረ።

ስለዚህ ጸሐፊ ማለት ሕግን የሚጽፍና የሚያስተምር ሰው ማለት ነው ። አሁን ይህ ምሳሌ ምን እንደሚያስተምረን እንመልከት ። መምህር ፥ ከመዝገቡ

አዲሱንና አሮጌውን ነገር የሚያወጣ ባለቤትን ይመስላል ይላል ። ባለቤት ተሞልቶ የተቈለፈ የመዝገብ ቤት አለው ። ከመዝገቡ ማንኛቸውንም ሲፈ ልግ ፣ ቤቱን ይከፍትና የሚፈልገውን ይወስዳል ። ከዚያ በኋላ ቤቱን እንደ ገና ይቈልፈዋል ። ባለቤቱ ተጨማሪ ዕቃ ደግሞ ሲፈልግ ፣ ይመለሰና ቁልፉን ከፍቶ ወደ ቤቱ ገብቶ ተጨማሪ ዕቃ ይወስዳል ። ከዚህ በኋላ እንደገና ቤቱን ይቈልፈዋል ።

ከቤቱ የሚያወጣው አንዳንድ ነገር አዲስ ነው ፤ አንዳንዱም አሮጌ ነው ። ኢየሱስ መምህርም እንደዚህ ነው ይላል ። የሚጽፍም ሰው ደግሞ እንደዚህ ነው ይላል ። አእምሮው የመዝገብ ቤቱ ነው ። ከአእምሮው አዲስ አሳብንና አሮጌ አሳብን ያወጣል ። ከእነዚህ አንዳንዶቹ አሳቦች በአእምሮው ለጥቂት ቀናት ወይም ለዓቶች ብቻ ኖረዋል ። ሌሎቹ አሳቦች በአእምሮው ለብዙ ወራት ወይም ዓመታት ኖረዋል ። ሲያስተምር ፣ እነዚህን አዲሰና አሮጌ አሳ ቦች በአንድ ላይ ያጣምራል ። ስለዚህ በአእምሮው ካለው አዲስና አሮጌ አሳብ ፣ ሌላ አዲስ አሳብን ይፈጥራል ።

ስለዚህ ስለ መንግሥተ ሰማያት ለማስተማር የሠለጠነ መምህር ፣ የመን ግሥተ ሰማያትን ምሳሌዎች ፣ በአእምሮው ካሉት ከአዲስና ከአሮጌ ነገሮች ያገኛል ። ኢየሱስ ምሳሌዎቹን ያገኘው እንደዚህ ነው ። መልካም መምህራን ሁሉ ምሳሌዎቻቸውን በዚህ መንገድ ያገኛሉ ። ምሳሌዎችን ለማግኘት ፣ አዲ ስና አሮጌ አሰረጂዎችን ያጣምራሉ ። ደግሞም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ ምሳሌዎች እንደ መንግሥተ ሰማያት አሰረጂዎች የተሠሩባቸው ታሪኮች ናቸው ። ስለዚህ ከባለቤቱ ምሳሌ ጥልቅ ትርጉሞች አንዱ ይህ ነው ። ኢየሱሰም ይህን ምሳሌ ከተናገረበት ምክንያቶች አንዱ ይህ ነው ።

(ማቴ. ፲፫ ፡ ፶፪ ተመልከት ።)

@et_christian_library

፫

# መንግሥተ ሰማያት የሚገቡ እነማን ናቸው ?



ኢየሱስ ብዙ ጊዜ ፡— ዛፍን ከፍሬዋ ለማወቅ ትችላላችሁ ብሎአል ። ደግሞም እንዲህ አለ ፡—

ከእሾህ ወይን መልቀም አይቻልም ፤ እሾህ የሚያፈራው እሾህን ብቻ ነውና ። ከእሾህ እሾህን እንጂ ወይንን ወይም አንዳችን ሌላ ነገር መልቀም አይቻልም ። ከኩርንችት በለስ መልቀም አይቻልም ። ኩርንችት የሚያፈራው ኩርንችትን ብቻ ነውና ። ከኩርንችት ኩርንችትን እንጂ በለስን ወይም አንዳችን ሌላ ነገር መልቀም አይቻልም ።

መልካም ዛፍ ሁሉ መልካም ፍሬ ያፈራል ። ዛፉ መልካም መሆኑን ከመልካም ፍሬው ታውቃላችሁ ።

ክፉም ዛፍ ክፉ ፍሬ ያፈራል ። ዛፉ ክፉ መሆኑን ከክፉ ፍሬው ታውቃላችሁ ።

መልካም ዛፍ ክፉ ፍሬ ማፍራት አይቻለውም ።

ክፉም ዛፍ መልካም ፍሬ ማፍራት አይቻለውም ።

መልካም ፍሬ የማያፈራ ዛፍ ሁሉ ይቈረጣል ። ወደ እሳትም ይጣላል ።

ኢየሱስ እንዲሁም ሰዎችን በሚያፈሩት ፍሬ ልናውቃቸው እንደምን ችል ይነግረናል ። መልካም ፍሬ የማያፈሩ ፣ መንግሥተ ሰማያት መግባት አይፈቀድላቸውም ።

ኢየሱስ እንዲህ አላቸው ፦ የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ ፣ ጌታ ሆይ ፣ ጌታ ሆይ ፣ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም ። በዚ ያን ቀን ብዙዎች ፦ ጌታ ሆይ ፣ ጌታ ሆይ ፣ በስምህ ትንቢት አልተናገርን ምን ? በስምህስ አጋንንትን አላወጣንምን ? በስምህስ ብዙ ተአምራት አላደረ ግንምን ? ይሉኛል ። የዚያን ጊዜም ፦ ከቶ አላወቅኋችሁም ፤ እናንተ ዓመፀ ኞች ፣ ከእኔ ራቁ ፣ ወደ መንግሥቴ ልትገቡ አይቻላችሁም ። እናንተ ክፉ የም ትሠሩ ከእኔ ራቁ ።

ኢየሱስ ክፉዎች መንግሥተ ሰማያት እንዲገቡ የማይፈቅደው ለምን ድር ነው ? እግዚአብሔር ዓመፀኞችን ከመንግሥተ ሰማያት ውጭ እንዲያደ ርጋቸው አስፈላጊ የሆነውስ ለምንድር ነው ? አስፈላጊ የሆነበት አንደኛው ምክንያት ፣ እግዚአብሔር ቅዱስ ነውና ኃጢአት በፊቱ እንዲኖር ስለማይፈ ልግ ነው ። ሁለተኛው ምክንያት ፣ ሰማይ አስደሳች ስፍራ ነውና ክፉዎች ከነ ዓመፃቸው ወደ መንግሥተ ሰማያት ሊገቡ አይፈቀድላቸውም ። እነርሱን ለመ ለየት አስፈላጊ የሆነበት ሁለቱም ምክንያቶች እነዚሁ ናቸው ። ነገር ግን ሌላ ምክንያት ደግሞ አለ ። ይህንም ከዚሁ ምሳሌ ልንረዳ እንችላለን ። አንድ የበሰበሰ ፍሬ ከሌሎች ፍሬዎች ጋር ቢደባለቅ ፣ ሌሎቹን ፍሬዎች መጥፎ ያደርጋቸዋል ። ስለዚህ ተለያይተው እንዲኖሩ ያስፈለገበት ምክንያት ይህ ነው ።

እግዚአብሔር ቅዱስ ነው ። ሰማይም ፍጹም ነው ። እርሱ በሚኖርበት ስፍራ ክፉዎች ከኖሩ ፣ ስፍራው ፍጹም ሊሆን አይችልም ። ክፉዎቹ በመልካ ሞቹ ላይ ጉዳት ቢያደርሱባቸው ፣ ሰማይ ፍጹም አይሆንም ። ስለዚህ እግዚአ ብሔር ቅዱስ ነውና ዓመፀኞችን ከመንግሥተ ሰማያት ውጭ ማድረግ አስፈ ለገ ። የእግዚአብሔርም ሰዎች እንዳይጐዱ ዓመፀኞችን ከመንግሥተ ሰማያት ውጭ ማድረግ አስፈለገ ።

(ማቴ. ፯ ፣ ፲፮—፳፫ ተመልከት ።)



@et_christian_library

፫

# የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ስለ ምን እንዳልጦሙ ።

በሦስቱ ወንጌሎች ማለት በማቴዎስ ፥ በማርቆስና በሉቃስ ውስጥ በት ንሽ ብቻ የሚለያዩ ዓረፍተ ነገሮች በብዙ ቦታ ይገኛሉ ። ይህንም ጉዳይ ለማስተዋል ሦስቱን ወንጌሎች ተራ በተራ እንመልከት ። ይህ የሚከተለው ታሪክ ማርቆስ እንደ ጻፈው ነው ፤—

የዮሐንስ ደቀ መዛሙርትና ፈሪሳውያን ይጦሙ ነበር ። መጥተውም ፦— የዮሐንስና የፈሪሳውያን ደቀ መዛሙርት የሚጦሙት የአንተ ደቀ መዛሙ ርት ግን የማይጦሙት ስለ ምንድር ነው ? አሉት ። ኢየሱስም አላቸው ፦— ሙሽራው ከእነርሱ ጋር ሳለ ሚዜዎች ሊጦሙ ይችላሉን ? ሙሽራው ከእነ ርሱ ጋር ሳለ ሊጦሙ አይችሉም ። ነገር ግን ሙሽራው ከእነርሱ የሚወሰድ በት ወራት ይመጣል ፥ በዚያ ወራትም ይጦማሉ ።

የሚከተለው ደግሞ ማቴዎስ እንደ ጻፈው ነው ፤—

በዚያን ጊዜ የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ወደ እርሱ ቀርበው ፦— እኛና ፈሪሳውያን ፥ ብዙ ጊዜ የምንጦመው ፥ ደቀ መዛሙርትህ ግን የማይጦሙት ስለ ምንድር ነው ? አሉት ። ኢየሱስም እንዲህ አላቸው ፦— ሚዜዎች ሙሽ ራው ከእነርሱ ጋር ሳለ ሊያዝኑ ይችላሉን? ነገር ግን ሙሽራው ከእነርሱ የሚወሰድበት ወራት ይመጣል ፥ በዚያ ጊዜም ይጦማሉ ።

ማቴዎስ ታሪኩን የሚነግረን እንደዚህ ነው ። ይህን ማርቆስ ከሚነግ ረን ጋር ስናነጻጽር ፥ ሁለቱም እንደሚቀራረቡ ለማየት እንችላለን ። በማርቆ ስና በማቴዎስ እነጋገር በጣም ትንሽ ልዩነት ብቻ ይገኛል ። ልዩነቱም በሚ ጠቀሙባቸው ቃላት ብቻ ነው ።

ማርቆስ ፦— መጥተውም ይላል ። ግን እነርሱ ማን እንደ ሆኑ በጣም አል ገለጣቸውም ። የመጡት ተራው ሕዝብ ወይም የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት እንደ ሆኑ አልገለጠም ። ማቴዎስ ግን ፦— የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ወደ እርሱ ቀርበው ይላል ። ይህ በእውነት ምንም ልዩነት አይባልም ። ምክንያቱም ፦— የዮሐንስ ደቀ መዛሙርትም ሕዝብ ናቸው ። ማቴዎስ ግን የዮሐንስን ደቀ መዛሙርት የጠቀሰበት ምክንያት ፥ በዚያን ጊዜ ዮሐንስ በእስር ቤት ስለ ነበር ነው ። ደቀ መዛሙርቱም የጦሙት ፥ በዚህ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም ።

ሌላው ልዩነት ደግሞ ማርቆስ ፦— ሙሽራው ከእነርሱ ጋር ሳለ ሚዜ ዎች ሊጦሙ ይችላሉን ? በሚልበት ቦታ ላይ ነው ። ማቴዎስ ግን ፦—

ሚዜዎቹ ሙሽራው ከእነርሱ ጋር ሳለ ሊያዝኑ ይችላሉን ? ይላል ። እዚህ ላይ የሚለያዩት በአንድ ቃል ብቻ ነው ። ማቴዎስ "ኀዘን" በሚል ቃል ሲጠቀም ፣ ማርቆስ ግን "ጦም" የሚለውን ቃል ተጠቀመበት ። አይሁድ ባዘኑ ጊዜ ይጦሙ ስለ ነበር ፣ ይህ በጣም አያስገርምም ።

ይህ የአይሁድ ልማድ ታሪኩን ያብራራልናል ። ኢየሱስ የሚለው ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ሰላለ ፣ ደቀ መዛሙርቱ ኃዘን የሰባቸውምና ሊጦሙ አይችሉም ነው ። እጅግ በጣም ተደስተው ነበር ። በሰርግ ላይ እንዳሉ እንግዶች ተደስተው ነበር ።

አሁን ይህንኑ ታሪክ በሉቃስ ወንጌል እንመልከት ። ይህን ታሪክ ማርቆስ ከሚነግረን ታሪክ ጋር ሰናነጸጽር ፣ ሁለቱም በጣም እንደሚቀራረቡ ለማየት እንችላለን ።

እነርሱም ፡— የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ስለ ምን ብዙ ይጦማሉ ጸሎትስ ስለ ምን ያደርጋሉ ፣ ደግሞም የፈሪሳውያን ደቀ መዛሙርት ስለ ምን እንደዚሁ ያደርጋሉ ፤ የአንተ ደቀ መዛሙርት ግን ይበላሉ ይጠጣሉም አሉት ። ኢየሱስም ፡— ሙሽራው ከእነርሱ ጋር ሳለ ሚዜዎችን ልታስጦሙ ትችላላችሁን ? ነገር ግን ወራት ይመጣል ፣ ሙሽራው ከእነርሱ ሊወሰድ ያን ጊዜ በዚያ ወራት ይጦማሉ አላቸው ።

በዚህ ነገር ላይ ሉቃስ ከማርቆስ ይለያል ። ሉቃስ ፡— የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ብዙ ይጦማሉ ጸሎትም ያደርጋሉ ይላል ። ጸሎትም ያደርጋሉ የሚለው ቃል ማቴዎስ ማርቆስም በሚነግሩን ታሪክ ውስጥ የለም ። ግን ይህ ልዩነት ነው ለማለት አይቻልም ። ምክንያቱም ፣ ሰዎቹ ሲጦሙ ጸሎትም አድርገዋል ። ሲጦሙ ሳለ ፣ ሁልጊዜም ጸሎት ያደርጉ ነበር ። ጦም ፣ ጸሎት የሚደረግበት አንድ መንገድ ነው ።

ኢየሱስ እዚህ ላይ ጦም ከጊዜው ጋር ተስማሚ መሆን አለበት እስ እንጂ መጦም በፍጹም አይገባም ብሎ አላስተማረም ። በዚያን ጊዜ ዮሐንስ ከደቀ መዛሙርቱ ተለይቶ በወኅኒ ቤት ታስሮ ስለ ነበር ፣ የእርሱ ደቀ መዛሙርት ጦሙ ። ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ተለይቶ የሚሰቀልበት ጊዜ እንደሚመጣ ገለጠ ። በዚያን ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ይጦማሉ ። ነገር ግን አሁን የክርስቶስ ቅዱስ መንፈስ ከእኛ ጋር ሁልጊዜ ስለሚሆን ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ሰንነጋገርና ሰንመላለስ በደስታ እንመላለን ። ኢየሱስ ሙሽራ ሆኖ በሚገኝበት ቦታ ሁሉ እንደ ተጋባዦች መደሰት ይገባናል ።

(ማቴ. ፱ ፣ ፲፬—፲፭ ፤ ማር. ፪ ፣ ፲፰—፳ ፤ ሉቃ. ፭ ፣ ፴፫ - ፴፭ ተመልከት ።)

# አዲሱና አሮጌው ።

ባለፈው ምዕራፍ ውስጥ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ለምን እንዳልጦሙ አየን ። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ ያልጦሙበት ምክንያት ፣ በሰርግ ላይ ሙሽራው አብሮአቸው እንዳለ ሚዜዎች ተደስተው ስለ ነበር ነው አለ ። ከዚያም በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ለምን እንዳልጦሙ ለመግለጥ ፣ ሁለት ሌላ አጫጭር ምሳሌዎች ተናገረ ። እነዚህ ምሳሌዎች በግብዣ ላይ ስለ ነበሩት ሚዜዎች ከተናገረው ምሳሌ በኋላ ይገኛሉ ። የመጀመሪያው ምሳሌ ይኸውና፡—

በአረጀ ልብስ አዲስ እራፊ የሚጥፍ የለም ፤ ቢደረግ ግን ፣ አዲሱ መጣፊያ አሮጌውን ይቦጭቀዋል ፣ መቀደዱም የባሰ ይሆናል ።

ኢየሱስ ይህን ምሳሌ ሲናገር ፣ ምን ማለቱ ነው ? አዲስ በአሮጌ ላይ መጣፍ የለበትም ማለቱ ነው ። በሕይወታችን ውስጥ ያለው አዲስ መንፈስ አዲስ አሠራር ያስፈልገዋል ማለቱ ነው ። ጦም የአሮጌው ሕይወት መግለጫ ክፍል ስለ ነበረ ፣ የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ጦሙ ። ነገር ግን ደስታ የአዲሱ ሕይወት መግለጫ ክፍል ስለ ነበረ ፣ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት በሉና ተደሰቱ ።

ኢየሱስ ያስተማረው ትምህርት እንደ አዲስ እራፊ ነበረ ። የዮሐንስ ወግ ግን እንደ አረጀ ልብስ ነበረ ። አዲስ እራፊ በአረጀ ልብስ ላይ ሊጣፍ አይቻልም ። ቢደረግ ግን ፣ መቀደዱ የባሰ ይሆናል ። እንደዚሁም አዲሱ የክርስቶስ መንገድ የአሮጌው ክፍል ሊሆን አይችልም ።

የፓለስቲና ሕዝብ በቀላል ሊያስተውሉት ስለ ቻሉ ፣ ይህ ኢየሱስ የተናገረው ምሳሌ በጣም ጥሩ ነበረ ። በዚያን ጊዜ አብዛኞቹ የፓለስቲና ሕዝቦች የተጣፈ ልብስ ይለብሱ ነበር ። ብዙ ጊዜም ልብስ ይጥፉ ነበር ። በዚያን ዘመን በእንዱ ልብስ ላይ አንድ መቶ ያህል የተጣፈ እራፊ ይታይ ነበር ። ነገር ግን አዲሱን እራፊ በአረጀው ልብስ ላይ ከመጣፋቸው በፊት ፣ ያጥቡት ነበር ። ባያጥቡት ግን ፣ ያልታጠበው አዲስ እራፊ ያረጀውን ልብስ ይቦጭቀዋል ፣ መቀደዱም በፊት ከተጣፈው የባሰ ይሆናል ።

ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ከመጀመሪያው የጠበቀ ምሳሌ ተናገረ ፤ እንዲህ ሲል ፡—

በአረጀ እቁማዳም አዲስ የወይን ጠጅ የሚያኖር የለም ፤ ቢደረግ ግን ፣ የወይን ጠጁ እቁማዳውን ያፈነዳል ፣ ወይኑም ጠጅ ይፈሳል ። እቁማዳውም

ይጠፋል ። አዲሱን የወይን ጠጅ ግን በአዲስ አቁማዳ ያኖራሉ ።

ኢየሱስ ይህን ሁለተኛውን ምሳሌ የተናገረው ለምንድር ነው ? በመጀመሪያው ምሳሌ ውስጥ የተጠቀሰው አዲስ እራፊ የአዲስ ጨርቅ ትንሽ ቍራጭ ብቻ ነው ። በዚህ በሁለተኛው ምሳሌ ግን አዲሱ የወይን ጠጅ በሙሉ አዲስ እንጂ ከአዲሱ አንድ ክፍል ብቻ አይደለም ። በአሮጌ ልብስ ላይ ያልታጠበ አዲስ እራፊ መጣፍ የማይገባ እንደ መሆኑ ፥ እንዲሁም አዲስ የወይን ጠጅ በአረጀ አቁማዳ ውስጥ ማኖርም ፈጽሞ አይገባም ። አዲስ የወይን ጠጅ በአረጀ አቁማዳ ውስጥ ቢደረግ ፥ አቁማዳው ይፈነዳል ። ከዚያ በኋላ የወይኑም ጠጅ አቁማዳውም ይጠፋሉ ። አዲስ የወይን ጠጅ በአዲስ አቁማዳ ውስጥ መኖር አለበት ።

እንዲሁም አዲስ አሳብ ፥ አዲስ ቅርጽም ዘዴም ሊኖሩት ይገባል ። አዲስ ነገር በአሮጌው አኳኋን ቢሠራበት ፥ ውድቀት ይከተለዋል። ስለዚህ ኢየሱስ በእነዚህ ምሳሌዎች ያስተማረው ፥ እርሱ የሚሰጠው አዲስ ሕይወት አዲስ አኗኗር የሚጠይቅ መሆኑን ነው ። ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው ፦— ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው ፤ አሮጌው ነገር አልፎአል ፤ እነሆ ፥ ሁሉም አዲስ ሆኖአል ።

አንዲት ወጣት ይህን ምሳሌ ስታነብ ፥ እንዲህ አለች ፦—

ይህ የሚናገረው ስለ እኔ ነው ። አዲስና የተሻለ አሳብ አለኝ ። ነገር ግን ገና አሮጌ ልማድን በመከተል ላይ ነኝ ። አንድን ነገር አምናለሁ ፤ ግን ሌላ ነገርን አደርጋለሁ ። ከአሁን ጀምሮ የማምነውን አደርጋለሁ ።

(ማር. ፪ ፥ ፳፩—፳፪ ተመልከት ።)

፲

## ሠራተኞች በወይን አትክልት ውስጥ እንደ ሠሩ ።



@et_christian_library

ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በፓለስቲና ሲመላለስ ፣ ብዙ የወይን አትክልት አየ ። አንድ ቀንም መንግሥተ ሰማያት ለወይኑ አትክልት ሠራተ ኞችን የቀጠረ ባለቤት ሰውን ትመስላለች ብሎ ለደቀ መዛሙርቱ ነገራ ቸው ።

ምሳሌው ይኸውና ፦ አንድ የወይን አትክልት ባለቤት ሠራተኞችን ሊቀጥር ከጠዋቱ በአሥራ ሁለት ሰዓት ወደ ገበያ ሄደ ። እርሱም በቀን አንድ ብር ሊከፍላቸው ተስማማና ሠራተኞቹ እንዲሠሩ ወደ ወይኑ አትክልት ሰደዳቸው ።

በሦስት ሰዓት ሌሎች ሠራተኞችን ሊቀጥር እንደገና ወደ ገበያ ሄደ ። በዚያም ሥራ የፈቱ ሌሎችን አግኝቶ ፦ እናንተ ደግሞ ወደ ወይኔ አትክ ልት ሂዱ ፤ የሚገባውንም እሰጣችኋለሁ አላቸው ። ሥራ የፈቱት ሰዎች ተስማሙና ተቀጠሩ ።

በስድስት ሰዓት ደግሞ ሌሎች ሠራተኞችን ሊቀጥር ወደ ገበያ ሄደ ። በዚያም ሥራ የፈቱ ሌሎች ቆመው አየ ። እንደገና ፦ እናንተ ደግሞ ሂዱ፣ በወይኔ አትክልት ሥሩ ፤ የሚገባውንም እሰጣችኋለሁ አላቸው ። እነዚያ ሥራ የፈቱት ሰዎች ተስማሙና ተቀጠሩ ።

ከሰዓት በኋላ በዘጠኝ ሰዓት ደግሞ ሥራ የፈቱ ሰዎች በገበያ ቆመው

እንደገና አገኘ ። እነርሱም በወይኑ አትክልት ለመሥራት ተስማሙና ተቀጠሩ ።

በአሥራ አንድ ሰዓት ደግሞ ሥራ የፈቱ ሌሎችን አገኘና ፦— ሥራ ፈት ታችሁ ቀኑን ሙሉ በዚህ ስለ ምን ትቆማላችሁ ? አላቸው ። እነርሱም ፦— የሚቀጥረን ስለ አጣን ነው አሉት ። እርሱም ፦— እናንተ ደግሞ ወደ ወይኔ አትክልት ሂዱ ። የሚገባውንም ትቀበላላችሁ አላቸው ።

በመሸም ጊዜ ፤ የወይኑ አትክልት ባለቤት ደመወዝ ሊከፍላቸው ሠራተ ኞቹን ሁሉ ጠራ ። በአሥራ አንድ ሰዓት ለገቡት ለእያንዳንዳቸው አንዳንድ ብር ከፈላቸው ። በዘጠኝ ሰዓት ለገቡትም ለእያንዳንዳቸው አንዳንድ ብር ከፈላቸው ። በስድስት ሰዓት ለገቡትም ለእያንዳንዳቸው አንዳንድ ብር ከፈላ ቸው ። በሦስት ሰዓት ለገቡትም ለእያንዳንዳቸው አንዳንድ ብር ከፈላቸው ።

ከጠዋቱ በአሥራ ሁለት ሰዓት የገቡትም አብዝተው የሚቀበሉ መስሎ አቸው ነበር ። ግን እነርሱ ደግሞ እያንዳንዳቸው አንዳንድ ብር ተቀበሉ ። ተቀብለውም በባለቤቱ ላይ ተቈጡና ፦— እኛ ቀኑን ሙሉ በፀሐይ ውስጥ በኃይል እየሠራን ውለን ለእነዚያ አንድ ሰዓት ለሠሩት ከእኛ እኩል ከፈልሃቸው አሉት ።

ባለቤቱም ከእነርሱ ለአንዱ እንዲህ አለው ፦— ወዳጄ ሆይ ፤ በአንድ ብር ቀኑን ሙሉ ለመሥራት ተስማማህ ። አልበደልሁህም ። ለምን ትቈጣለህ? በገበያ ቀኑን ሙሉ ሥራ ፈተው ለነበሩት ለእነዚህ ስዎች ደግ ለመሆን ወደ ድሁ ። እነርሱ ፦— ሥራ ወይም ለልጆቻቸው ምግብ አልነበራቸውም ። እኔ መልካም ስለ ሆንሁ ፤ መቈጣት የለብህም ። የተስማማህበትን ውሰድና ሂድ ።

(ማቴ. ፳ ፤ ፩—፲፮ ተመልከት ።)

## ፲፩

# የታማኙና የሃኬተኛው አገልጋይ ምሳሌ ።



ኢየሱስ በኖረበት አገር የነበሩ ባለ ጠጎች አንዳንድ ጊዜ ወደ ሩቅ አገር ይሄዱ ነበር ። ሲሄዱም አብዛኛውን ጊዜ ንብረታቸውን ለባሮቻቸው አደራ ይሰጡ ነበር ። ኢየሱስ ሩቅ አገር ስለ ሄደው መኰንን ይህን ምሳሌ ተናገረ ።

ባለ ጠጋው መኰንን አገልጋዮቹን ጠርቶ ፦ እኔ ወደ ሌላ አገር እሄዳለሁ ። ገንዘቤን በጥንቃቄ እንድትጠብቁት እፈልጋለሁ አላቸው ። አን ደኛውን አገልጋይ ፦ አምስት ሺህ ብር እንካ ። አምስት ሺህ ብር ብዙ ገንዘብ ነው ። በጥንቃቄ ጠብቀው ። ነግድበትና አትርፍ ብሎ አዘዘው ።

ሁለተኛውን አገልጋይም ፦ ሁለት ሺህ ብር ይኸውና ። ይህ ብዙ ገንዘብ ነው ። በጥንቃቄ ጠብቀው ። ነግድበትና አትርፍ ብሎ አዘዘው ። ለሦስተኛው አገልጋይም አንድ ሺህ ብር ሰጠው ። እንዲህም ብሎ አዘዘው ፦ ይህ ብዙ ገንዘብ ነው ። በጥንቃቄ ጠብቀው ። ነግድበትና አትርፍ ።

ከዚህ በኋላ ባለ ጠጋው ወደ ሌላ አገር ሄደ ። አምስት ሺህ ብር የተሰ ጠው አገልጋይ እንዲህ ብሎ አሰበ ፦ ይህ ብዙ ገንዘብ ነው ። ብነግድበት አምስት ሺህ ብር ትርፍ ሳላገኝ አልቀርም ። እንደዚህ ባደርግ ፤ ጌታዬን ከሄደበት አገር ሲመለስ ፤ ደስ ያሰኘዋል ። ስለዚህ በዚያ ገንዘብ ነገደ ። ሁለተኛውም አገልጋይ ፦ ይህ ብዙ ገንዘብ ነው ። እነግድበትና አተርፋለሁ ብሎ አሰበ ። በሁለቱ ሺህ ብርም ነገደ ።

አንድ ሺህ ብር የተሰጠው አገልጋይ ግን ፦ ጌታዬ ጨካኝ ሰው ነው ። እፈራዋለሁ ። በዚህ ገንዘብ በመነገድ ፈንታ እቀብረዋለሁ ብሎ አሰበ ። ስለዚህ በዚያ ገንዘብ በመነገድ ፈንታ ጉድጓድ ቈፈረና ገንዘቡን ቀበረ ።

ከብዙ ዘመንም በኋላ መኰንኑ ከሄደበት አገር ተመለሰ ። አገልጋዮቹንም ጠራና ፦ ገንዘቡን እንደ ምን ተጠቀማችሁበት ? ብሎ ጠየቃቸው ።

የመጀመሪያው አገልጋይ ፦ አምስት ሺህ ብር ሰጠኸኝ ። ነገድሁበት አምስት ሺህ ብርም አተረፍሁ ብሎ መለሰ ። ጌታውም ፦ መልካም ፣ አንተ በጎ ታማኝም አገልጋይ ፤ በጥቂቱ ታመነሃል ፣ በብዙ እሾምሃለሁ ። ወደ ጌታህ ደስታ ግባ አለው ።

ሁለተኛውም አገልጋይ ወደ ጌታው ቀርቦ ፦ ሁለት ሺህ ብር አተረፍሁ አለው። ጌታውም ፦ መልካም ፣ አንተ በጎ ታማኝም አገልጋይ ፤ በጥቂቱ ታመነሃል ፣ በብዙ እሾምሃለሁ ። ወደ ጌታህ ደስታ ግባ አለው ።

አንድ ሺህ ብር የተቀበለው አገልጋይም ቀርቦ ፦ ካልዘራህባት የምታጭድ ካልበተንህባትም የምትሰበስብ ጨካኝ ሰው መሆንህን አውቃለሁ ። ፈራሁም ። ስለዚህ ወደ ሌላ አገር ከሄድህ በኋላ ፣ ገንዘብህ እንዳይጠፋ ጉድጓድ ቈፍሬ ቀበርሁት ። ልክ አንድ ሺህ ብር ይኸውልህ አለው ።

ጌታውም መልሶ እንዲህ አለው ፦ አንተ ክፉና ሃኬተኛ አገልጋይ ። ካልዘራሁባት እንዳጭድ ካልበተንሁባትም እንድሰበስብ ታውቃለህን ? በገንዘቤ ነግደህ ማትረፍ ነበረብህ ። በማትረፍ ፈንታ ገንዘቤን ቀበርኸው ። ከዚህ በኋላ አንዱን ሺህ ብር ወሰደበትና ለታማኙ አገልጋይ ሰጠው ።

ባለ ጠጋው ቀጥሎ እንዲህ አለ ፦ ያለውን ነገር በደኅና የሚጠቀምበት ሌላ ይሰጠዋል ። ይበዛለትማል ። ያለውን ነገር የማይጠቀምበት ግን ፣ ያለው እንኳ ይወሰድበታል ። ለምንም ነገር የማይረባውን አገልጋይ ከቤት አባርሩ ።

(ማቴ. ፳፭ ፣ ፲፬—፴ ተመልከት ።)

@et_christian_library

## ፲፪

# የዓመፀኛው መጋቢ ምሳሌ ።

የሉቃስ ወንጌል አንድ ታማኝ ስላልነበረ መጋቢ ይነግረናል ። መጋቢ ማለት አስተዳዳሪ ወይም ሥራ አስኪያጅ ማለት ነው ።

ኢየሱስ እንዲህ የሚል አንድ ምሳሌ ተናገረ ፦ መጋቢ የነበረው አንድ ባለ ጠጋ ነበረ ። ይህ መጋቢ የባለ ጠጋው ንብረት ኃላፊ ነበረ ። አንድ ቀን ባለ ጠጋው ፤ መጋቢው ንብረቱን እንደሚበትን ሰማ ። ስለዚህ ባለ ጠጋው መጋቢውን ጠርቶ ፦ ይህ የምሰማብህ ምንድር ነው ? ታማኝ አይደለህም ። መልካም አስተዳዳሪ ወይም ሥራ አስኪያጅ አይደለህም ። ንብረቴን ታጠፋለህ ። ታማኝ አይደለህም ። አዲስ መጋቢ እቀጥራለሁ ። የመጋቢነትህን ሂሳብ አስረክበኝ አለው ።

በዚህ ጊዜ መጋቢው በልቡ እንዲህ አለ ፦ ምን ላድርግ ? ጌታዬ ሥራዬን ከእኔ ሊወስድ ነው ። ሥራ አጣለሁ ። ለመቈፈር ኃይል የለኝም ፤ መለመንም አፍራለሁ ። ከዚያም ጥቂት አሰበና እንዲህ አለ ፦ የማደርገውን አውቃለሁ ። የጌታዬን ባለ ዕዳዎች እረዳለሁ ። ሥራ ስፈታም ፥ በቤታቸው ይቀበሉኛል ። ከዚያ ወዲያ እንደ ቀን ሠራተኛ መቈፈር አያስፈልገኝም ። መለመን አያስፈልገኝም ። አፍረትም ውስጥ አልገባም ። የጌታዬን ባለ ዕዳዎች እያንዳንዳቸውን እጠራና ለጌታዬ ምን ያህል ዕዳ እንዳለባቸው እጠይቃለሁ ። ከዕዳውም ግማሹን ብቻ እንዲከፍሉ አደርጋለሁ ። ሂሳቡንም እናስተካክላለን ።

ስለዚህ የመጀመሪያውን ባለ ዕዳ ጠርቶ ፦ ለጌታዬ ምን ያህል ዕዳ አለብህ ? ብሎ ጠየቀው ።

ባለ ዕዳውም ፦ መቶ ማድጋ ዘይት አለ ።

መጋቢውም ፦ ደብዳቤህን እንካ ፈጥነህም ተቀምጠህ አምሳ ብለህ ጻፍ ። አሁን አምሳ ማድጋ ዘይት ብቻ ክፈል ። ይህም ዕዳህን ይጨርስልሃል አለው ።

ባለ ዕዳው ካለበት ዕዳ ግማሹን ብቻ ስለ ከፈለ ፥ ተደሰተ ። መጋቢውም አላፈረም ።

በኋላም ሌላውን ባለ ዕዳ ፦ ምን ያህል ዕዳ አለብህ ? ብሎ ጠየቀው ።

ባለ ዕዳውም ፦ መቶ ጫን ስንዴ አለው ።

መጋቢውም ፦— እባክህ ደብዳቤህን እንካ ፈጥነህም ተቀምጠህ ስማንያ ሜን ስንዴ ብለህጻፍ ። አሁን ስማንያ ሜን ስንዴ ብቻ ዕዳ አለብህ እንጂ መቶ አይደለም ። ስለዚህ አሁን ስማንያ ሜን ስንዴ ብቻ እንድትከፍለኝ እለምንሃለሁ ። ይህም ዕዳህን ይጨርስልሃል አለው ። ባለ ዕዳውም ከዕዳው ስማንያ ብቻ በመክፈሉ ተደሰተ ።

ጌታው ያልታመነው መጋቢ ያደረገውን በሰማ ጊዜ ፣ ጠርቶ ፦—

ይህን የመጋቢነትህን ሂሳብ በእንደዚህ ዓይነት መንገድ ስላስተካከልህ ፣ ልባም ነህ ። ምክንያቱም ፣ በዚህ አደራረግህ ብዙ ወዳጆች ለራስህ ታደርጋለህ አለው ።

በኋላም ኢየሱስ ከምሳሌው የሚገኘውን ትምህርት ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ ሲል ገለጠላቸው ፦— መጋቢው ታማኝ አልነበረም ። ነገር ግን ስለ ራሱ ዓለማዊ ጥቅም ባደረገው ጥንቃቄ ልባም ነበረ ። እርሱ ለዓለም ነገር እንዲህ ልባም ሲሆን ፣ የእግዚአብሔር ልጆች ለዘላለማዊ ቤታቸው ምንኛ ልባሞች ሲሆኑ ይገባቸዋል ።

ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን እንዲህ ብሎ መከራቸው ፦— በዓለማዊ ገንዘብ ወዳጆችን ለራሳችሁ አድርጉ ፤ ዓለማዊ ገንዘብ ያልቃልና ። ገንዘብን በልባምነት ብትጠቀሙበት ፣ ሰዎችን በመርዳት ወዳጆችን ለራሳችሁ ብታደርጉም ፣ እነርሱ በዘላለም ቤቶች ይበቀሉአችኋል አታፍሩምም ።

(ሉቃ. ፲፮ ፣ ፩—፱ ተመልከት ።)



፲፫

ክፉው አገልጋይ ።

@st_christian_library

አንድ ቀን ከኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ጴጥሮስ የሚባለው ወደ ኢየሱስ ቀርቦ ፦— ጌታ ሆይ ፣ ወንድሜ ቢበድለኝ ስንት ጊዜ ልተውለት ? እስከ ሰባት ጊዜን ? ብሎ ጠየቀው ። ጴጥሮስ ፦— ሰባት ጊዜን ? ብሎ የጠየቀበት ምክንያት፣ ሰባት በእርሱ ዘንድ ብዙ በመሆኑ ነው ። ደግሞም በዚያን ዘመን ሰባት ሙሉነትንና ፍጹምነትን የሚያመለክት ቊጥር ተደርጎ ይታይ ስለ ነበረ ነው ። ኢየሱስ ግን ፦— እስከ ሰባ ጊዜ ሰባት እንጂ እስከ ሰባት ጊዜ አልልህም ብሎት የሚከተለውን ምሳሌ ተናገረ ።

መንግሥተ ሰማያት አገልጋዮቹን ሊቈጣጠር የወደደን ንጉሥ ትመስላለች ። እልፍ መክሊት ዕዳ ያለበትን አንድ ሰው ወደ እርሱ አመጡ ። (ኢየሱስ በዚህ ምድር በተመላለሰበት ዘመን ፣ አንድ መክሊት እንደ አንድ ሺህ ብር የሚያገለግል ነበር ።) እልፍ መክሊትን ሊከፍል አልቻለም ። ስለ ዚህ እርሱና ሚስቱ ልጆቹም ያለውም ሁሉ እንዲሸጥና ዕዳው ሁሉ እንዲከፈል ጌታው አዘዘ ። ስለዚህ አገልጋዩ ወድቆ ሰገደለትና ፦— ጌታ ሆይ ፣ ታገሠኝ ሁሉንም እከፍልሃለሁ አለው ። የዚያም አገልጋይ ጌታ አዘነለትና ለቀቀው ። ዕዳውንም ተወለት ። ነገር ግን ያ አገልጋይ ወጥቶ ከባልንጀሮቹ ከአገልጋዮቹ መቶ ዲናር ዕዳ ያለበትን አንዱን አገኘ ። (አንድ ዲናር አንድ ብር ያህል ነው ።) ያዘው አንቆም ፦ መቶ ዲናር ዕዳህን ክፈለኝ አለው ። ስለዚህ ባልንጀራው አገልጋይ ወድቆ ታገሠኝ ሁሉንም እከፍልሃለሁ ብሎ ለመነው ። እርሱ ግን እምቢ አለው ። ወስዶ ዕዳውን እስኪከፍል ድረስ በወኅኒ አኖረው ።

ባልንጀሮቹ የሆኑ አገልጋዮችም ያደረገውን አይተው እጅግ አዘኑ ፣ መጥተውም የሆነውን ሁሉ ለጌታቸው እንዲህ ብለው ገለጡ ፦— አንተ እልፍ መክሊት ዕዳ ያለበትን አገልጋዩን ባልንጀራችንን ለቀቅህ ። ነገር

@et_christian_library

ግን እርሱ ክፉ ሰው ነው ። ለአንድ መቶ ዲናር ብቻ ባለ ዕዳው የሆነውን የባልንጀራውን ዕዳ መተው እምቢ አለ ። ባልንጀራውን መማር እምቢ አለ ። አንቀውና ዕዳውን እስኪከፍል ድረስ በወኅኒ አኖረው ።

ከዚያ ወዲያ ጌታው ክፉውን አገልጋይ ጠርቶ አለው ፦ አንተ ክፉ አገ ልጋይ ፣ ማረኝ ብለህ ስለ ለመንኸኝ ለቀቅሁህ ያንም ታላቅ ዕዳ ተውሁት። አንተ ግን ክፉ አገልጋይ ነህ ። እኔ እንደ ማርሁህ ፣ ባልንጀራህ የሆነውን ያን አገልጋይ ልትምረው ለአንተስ አይገባህምን? እርሱን መማር እምቢ አልህና በወኅኒ አኖርኸው ።

ጌታውም ተቈጣና ወታደሮቹን ፦ መማር እምቢ ስላለ ፣ ዕዳውን ሁሉ እስኪከፍል ድረስ ፣ በወኅኒ አኑሩት አለ ። ስለዚህ ወታደሮቹ አንቀው በወ ኅኒ አኖሩት ።

ኢየሱስም ፦ ከእናንተ እያንዳንዱ ወንድሙን ከልቡ ይቅር ካላለ ፣ እን ዲሁ ደግሞ የሰማዩ አባቴ ያደርግባችኋል አለ ።

(ማቴ. ፲፰ ፣ ፳፫—፴፭ ተመልከት ።)

፲፩

# ባለ ጠጋው ሰውና አልዓዛር ።

ከቀጭን የተልባ እግር የተሠራ ቀይ ልብስ የሚለብስ አንድ ባለ ጠጋ ሰው ነበረ ። (ከቀጭን የተልባ እግር የተሠራ ቀይ ልብስ የዚያን ዘመን ነገሥታት የሚለብሱት ልብስ ነው ።) በጣም ባለ ጠጋ ሰው ስለ ነበረ ፣ እንደ ንጉሥ ለብሶ በየዕለቱ በምቾት ይኖር ይበላም ይጠጣም ነበር ።

አልዓዛር የሚባል አንድ ድሀ ሰውም በደጁ ይተኛ ነበር ። ይህ ሰው ከዚህ ባለ ጠጋ ማዕድ ከሚወድቀው ፍርፋሪ ሊጠግብ ይመኝ ነበር ። አካሉም በሙሉ በቍስል ተሣቀየ ። ሁልጊዜም በባለ ጠጋው ደጅ ይተኛ ነበር። ቍስሉ እየባሰ ሲሄድም ፣ ከባለ ጠጋው ደጅ ለነበሩት ውሾች ተተወ እንጂ ማንም አልረዳውም ። እነዚህም ውሾች ጨካኞችና መጥፎዎች ነበሩ ። ቀርበው ቍስሉን ሲልሱት ፣ ሊያባርራቸው አልቻለም ። በድካምና በሥቃይ ተይዞ ስለ ነበር ፣ አላባረራቸውም ።

በመጨረሻም በረሃብና በቍስል ተሣቅይቶ ሞተ ። መላእክትም አብርሃም ወዳለበት ወሰዱት ። ባለ ጠጋውም ሞተ ። ከቀጭን የተልባ እግር የተሠራውንም ቀይ ልብስ ለብሶ ተቀበረ ። ነገር ግን ነፍሱ ወደ ሲኦል ሄዳ ተሣቀየች ። አሻቅቦም አልዓዛርን ከአብርሃም ጋር በሩቅ አየው ። በኋላም እየጮኸ ፡— አብርሃም አባት ሆይ ፣ ማረኝ ። በዚህ ነበልባል እሣቀያለሁና የጣቱን ጫፍ በውኃ ነክሮ መላሴን እንዲያበርድልኝ አልዓዛርን ስደድልኝ አለ ።

አብርሃም ግን እንዲህ ብሎ መለሰለት ፡—

ልጄ ሆይ ፣ አንተ በሕይወትህ ሳለህ መልካም እንደ ተቀበልህ አስብ ፤ አልዓዛርም እንዲሁ ክፉ ። ውሾች በመላሳቸው ቍስሉን ይልሱት ነበር ። አንተ አልመገብኸውም ወይም አላሰብህለትም ። አሁን እርሱ በዚህ ይጸናናል ። አንተም በሲኦል ትሣቀያለህ ። ከዚህም ሁሉ ጋር ከዚህ ወደ እናንተ ሊያልፉ የሚፈልጉ እንዳይችሉ ፣ ወዲያ ያሉ ደግሞ ወደ እኛ እንዳይሻገሩ ፣ በእኛና በእናንተ መካከል ታላቅ ገደል ተደርጎአል ።

በሲኦል ሥቃይ ያለው ባለ ጠጋ ሰውም እንዲህ አለ ፡— እንኪያስ ፣ አብርሃም አባት ሆይ ፣ አልዓዛርን ወደ አባቴ ቤት እንድትሰደው እለምንሃለሁ ። አምስት ወንድሞች አሉኝ ። አልዓዛርም ንስሐ ግቡ ብሎ እንዲመክራቸው ስደደው ። እግዚአብሔርን እንዲታዘዙ ይምከራቸው ። ድሆችን እንዲረዱ ይምከራቸው ። ወደ ሲኦል ገብተው እንዳይሣቀዩ ሕይወታቸውንም እንዲለውጡ ያስጠንቅቃቸው ።



@et_christian_library

አብርሃም ግን ፡—እነርሱ ሙሴና ነቢያት አሉአቸው ። ሙሴን ይስሙት። ነቢያትንም ይስሙአቸው አለው ።

በሲኦል ያለው ሰውም ፡— አይደለም ፤ አብርሃም አባት ሆይ ፤ ነገር ግን ከሙታን አንዱ ቢሄድላቸው ፤ ንስሐ ይገባሉ አለ ።

አብርሃምም ፡— ሙሴን ይስሙት ። ሙሴንና ነቢያትንም የማይሰሙ ከሆነ ፤ ከሙታንም አንኳ አንድ ቢነሣ አያምኑም አለው ።

(ሉቃ. ፲፮ ፤ ፲፱—፴፩ ተመልከት ።)

፲፫

# ሰነፉ ባለ ጠጋ ሰው ።



አንድ ቀን አንድ ሰው ወደ ኢየሱስ መጣና ፡— መምህር ሆይ ፡ አባታችን የተወልንን ርስት ከእኔ ጋር እንዲካፈል ለወንድሜ ንገረው ። ወንድሜ ከእኔ ጋር ምንም አልካፈልም ብሎአልና አለው ።

ኢየሱስም ፡— ፈራጅና አካፋይ በላያችሁ እንድሆን ማን ሾመኝ ? አለው ። ከዚያም ሕዝቡን ፡— የሌሎችን ንብረት እንዳትመኙ አስጠነቅቃችኋለሁ ። መመኘትና መሰሰት ኃጢአት ነው ። የሰው ሕይወት በገንዘቡ ብዛት አይደለምና የሌሎችን ንብረት ከቶ አትመኙ አላቸው ።

በኋላም ይህን የሚከተለውን ምሳሌ እንዲህ ብሎ ተናገረ ፡—

የአንድ ባለ ጠጋ ሰው እርሻ እጅግ ፍሬያማ ሆነችለት ። እርሱም ፡— ፍሬዬን የማከማችበት ስፍራ አጥቻለሁና ምን ላድርግ ? ብሎ በልቡ አሰበ ። እንዲህ አደርጋለሁ ፤ ጐተራዬን አፍርሼ ሌላ የሚበልጥ እሠራለሁ ፤ በዚያም ፍሬዬንና በረከቴን ሁሉ አከማቻለሁ አለ ።

ከዚህም በኋላ ነፍሱን ፡— አንቺ ነፍሴ ፡ ለብዙ ዘመን የሚቀር ብዙ በረከት አለሽ ፤ ዕረፊ ፤ ብዪ ፤ ጠጪ ፡ ደስ ይበልሽ አላት ።

እግዚአብሔር ግን ፡— አንተ ሰነፍ ፡ በዚች ሌሊት ነፍስህን ከአንተ ሊወስዱአት ይፈልጓታል ። ነፍስህ ሊፈረድባት በእግዚአብሔር ፊት ትቀርባለች። ይህስ የሰበሰብኸው ለማን ይሆናል ? ሰነፍ ነበርህ አለው ።

ከዚያም በኋላ ኢየሱስ ፦— ለራሱ ገንዘብ የሚያከማች ፥ በእግዚአብሔር ዘንድም ባለ ጠጋ ያልሆነ ሰው ልክ እንደዚያ ሰነፍ ነው አለ ።

ሰው ያለው ሁሉ ከእግዚአብሔር የተቀበለው ነው ። ንብረታችንም ሁሉ እግዚአብሔር የሰጠን ስጦታ ነው ። ስለዚህ ንብረታችንን ለእግዚአብሔር መንግሥት ክብርና ለሰው ችግር ማቃለያ እንጂ ለራሳችን ብቻ ልንጠቀም በት አይገባም ። እግዚአብሔር የሰጠንን ሁሉ እንድናስረክብ ፥ በማንኛውም ጊዜ ይጠይቀን ይሆናል ። ስለዚህ ንብረታችንን ከእግዚአብሔርና ከሰዎች ጋር እንካፈል ። የባልንጀራችንን ንብረት አንመኝ ። በዚህ ምሳሌ እንደ ተነገ ረን ሰነፍ ባለ ጠጋ አንሁን ። ማንም ሰው በንብረቱ ድሆችን ካልረዳ ፥ እንደ ዚያ ሰው ሰነፍ ነው ። ማንም ሰው የጐረቤቱን ንብረት ቢመኝ ፥ ሰነፍ ነው ።

ከአሥርቱ ትእዛዛትም የመጨረሻው አትመኝ ይሰኛል ።

(ሉቃ. ፲፪ ፥ ፲፫—፳፩ ተመልከት ።)



## ፲፮

## መልካሙ ባልንጀራ ።

@ethchristian_library

አንድ ቀን አንድ ሕግ አዋቂ ኢየሱስን ሊፈትነው ፈለገና ፦ መምህር ሆይ ፣ የዘላለምን ሕይወት እንድወርስ ምን ላድርግ ? አለው ።

ኢየሱስም ሕግ አዋቂውን ፦ በሕግ የተጻፈው ምንድር ነው ? የምታነበውስ ምንድር ነው ? አለው ።

ሕግ አዋቂውም መልሶ ፦ ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም ኃይልህም በፍጹም አሳብህም ውደድ ፣ ባልንጀራህንም እንደ ራስህ ውደድ አለው ።

ኢየሱስም ፦ እውነት መለስህ ፤ የተጻፈውን አድርግ በሕይወትም ትኖራለህ አለው ።

ነገር ግን ሕግ አዋቂው የተጻፈውን እንደ ታዘዘ ለሰዎች ለማሳየት ፈለገ ። ራሱን ሊያጸድቅ ወደደ ። ስለዚህም ኢየሱስን ፦ ባልንጀራዬስ ማን ነው ? ብሎ ጠየቀው ። ኢየሱስም ይህን ምሳሌ እንዲህ ብሎ ነገረው ፦ አንድ ሰው ከኢየሩሳሌም ወደ ኢያሪኮ ወረደ ፤ በወንበዴዎችም እጅ ወደቀ ። እነርሱም ገፈፉት ደበደቡትም በሕይወትና በሞት መካከል ትተውት ሄዱ ።

ድንገትም አንድ ካህን በዚያ መንገድ ከኢየሩሳሌም ወደ ኢያሪኮ ሲወርድ ፣ የቈሰለውን ሰው አይቶት ገለል ብሎ አለፈ ። እንዲሁም ደግሞ አንድ ሌዋዊ በዚያ መንገድ ከኢየሩሳሌም ወደ ኢያሪኮ ወረደ ። ወደዚያ ስፍራ ደረሰና የቈሰለውን ሰው አይቶት ገለል ብሎ አለፈ ። በድንገትም አንድ ሳምራዊ (ሳምራውያን ከአይሁድ ወገን አልነበሩም ።) ከኢየሩሳሌም ወደ ኢያሪኮ ሲወርድ ፣ ወደ እርሱ ደረሰ ። የቈሰለውን ሰው አይቶም አዘነለት ። በዚህ ጊዜ ወንበዴዎቹ በድንገት ሊመለሱ ይችሉ ነበር ። ነገር ግን ሳምራዊው ለቈሰለው ሰው አዝኖለት ስለ ነበር ፣ ወንበዴዎቹን አልፈራም ። ቀርቦም ዘይትና



ወስዶው ጠበቀውም ። በማግሥቱም ሁለት ዲናር አውጥቶ ለባለቤቱ ሰጠና፡-

የወይን ጠጅ አውጥቶ በቍስሎቹ ላይ አፈሰሰ ። ታላቅ ርኅራኄ ስለ ነበረው ፥ ቍስሎቹን በማጠብ ያለውን የወይን ጠጅ ሁሉ ጨረሰ ። የወይኑም ጠጅ ቍስሉን ንጹሕ አድርጎ አጠበው ። ዘይቱም ከቍስሎቹ ሥቃይ አሻለው ። ከዚያም በኋላ ቍስሎቹን አሰሮ በራሱ አህያ ላይ አስቀምጦ ወደ እንግዶች ማደርያ



ወስደው ጠበቀውም ። በማግሥቱም ሁለት ዲናር አውጥቶ ለባለቤቱ ሰጠና፦

ጠብቀው ፥ ከዚህም በላይ የምትከስረውን ሁሉ እኔ ስመለስ እከፍልሃለሁ አለው ። ከዚህ በኋላም ሳምራዊው ከእንግዶቹ ማደርያ ወጥቶ ጕዞውን ቀጠለ ።

ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ሕግ አዋቂውን ፦ እንግዲህ ከእነዚህ ከሦስቱ በወንበዴዎች እጅ ለወደቀው ባልንጀራ የሆነው ማንኛው ይመስልሃል ? ብሎ ጠየቀው ።

ሕግ አዋቂውም ፦ ምሕረት ያደረገለት ሰው ነው ባልንጀራ የሆነው አለ ።

ኢየሱስም ፦ ሂድ አንተም እንዲሁ አድርግ አለው ።

(ሉቃ. ፲ ፥ ፴፫—፴፯ ተመልከት ። )

## ፲፯

# የግብዣው ምሳሌ ።

በአንድ ሰንበት አንድ አለቃ ኢየሱስን ምሳ ጋበዘው ። ኢየሱስ በአለቃው ቤት ተቀምጦ ሳለ ፣ ሌሎች የተጋበዙት እንግዶች ሲገቡ ያይ ነበር ። እነዚያ የተጋበዙት የከበሬታ ከፍራ እንደ መረጡ ተመልክቶ ይህን ምሳሌ ተናገረ ፡—

ማንም ለሰርግ ቢጠራህ ፣ በከበሬታ ስፍራ አትቀመጥ ፤ ምናልባት ከአንተ ይልቅ የከበረ እንግዳ ተጋብዞ ይሆናልና ። ከአንተ ይልቅ የከበረ እንግዳ ሲመጣ ፣ አንተንም እርሱንም የጋበዘ መጥቶ ፡— ስፍራህን ለዚህ ሰው ስጥና በዝቅተኛ ስፍራ ተቀመጥ ይልሃል ። በዚያም ጊዜ በዝቅተኛው ስፍራ ስትቀመጥ ፣ ታፍራለህ ። አንተ ግን በተጋበዝህ ጊዜ ፣ ራስህን ዝቅ አድርገህ ሂድና በዝቅተኛው ስፍራ ተቀመጥ ። የጠራህም ሲመጣ ፡— ወዳጄ ሆይ ፣ በዝቅተኛው ስፍራ ለምን ትቀመጣለህ ? እባክህ ወደ ክብር ስፍራ ውጣ ይልሃል ። በዚያን ጊዜ በሌሎቹ እንግዶችና በጠራህ ትከበራለህ ። ራሱን የሚያከብር ሁሉ ይዋረዳልና ፣ ራሱንም የሚያዋርድ ሁሉ ይከብራል ።

ከዚህ በኋላ ኢየሱስ አለቃውን እንዲህ ፣ አለው ፡— የምሳ ወይም የእራት ግብዣ ባደረግህ ጊዜ ፣ ወዳጆችህን ወይም ወንድሞችህን ወይም ዘመዶችህንም ባለ ጠጎች ጎረቤቶችህንም አትጥራ ። ብትጠራቸው ፣ እነርሱ ደግሞ በተራቸው ምናልባት ይጠሩሃል ብድራትም ይመልሱልሃል ። ነገር ግን ግብዣ ባደረግህ ጊዜ ፣ ድሆችንና ጉንድሾችን አንካሶችንም ዕውሮችንም ጥራ ። ብፁዕ ትሆናለህ ። ምክንያቱም ፣ የሚመልሱት ብድራት የላቸውም ። ጌታ ራሱም በጻድቃን ትንሣኤ ይመልስልሃል ።

ከተቀመጡትም አንዱ ይህን ሰምቶ ፡— በእግዚአብሔር መንግሥት እንጀራ የሚበላ ብፁዕ ነው አለው ።

ኢየሱስ ግን እንዲህ አለው ፡— አንድ ሰው ታላቅ እራት አድርጎ ብዙዎችን ጠራ ። በእራትም ሰዓት የተጋበዙትን ፡— አሁን ተዘጋጅቶአልና ኑ እንዲላቸው አገልጋዩን ላከ ።

ነገር ግን ሁላቸውም በአንድነት ያመካኙ ጀመር ። የፊተኛው ፡— መሬት ገዝቼአለሁ ወጥቼም ላየው በግድ ያስፈልገኛል ፤ ይቅር እንድትለኝ እለምንሃለሁ አለው ።

ሌላውም ፡— አምስት ጥምድ በሬዎች ገዝቼአለሁ ልፈትናቸውም

እሄዳለሁ ፤ ይቅር እንድትለኝ እለምንሃለሁ አለው ። ሌላውም ፡— ሚስት አግብቼአለሁ ስለዚህም ልመጣ አልችልም አለው ።

አገልጋዩ ተመልሶ ጌታውን እንዲህ አለው ፡— የታደሙ እንግዶች ሁሉ ይቅርታ እንድታደርግላቸው ለምነውሃል ። አንዱ መሬት ገዝቶአልና ሊያየው ግድ አስፈለገው ። ሌላውም በሬዎች ገዝቶአልና በሬዎቹን ሊፈትናቸው ሄዶአል ። ሌላው ደግሞ ሚስት አግብቶአልና ሊመጣ አልቻለም ።

በዚያን ጊዜ ጌታው ተቈጥቶ አገልጋዩን እንዲህ አለው ፡— መሬት ፣ በሬዎች ፣ ሚስት ፣ እነዚህ ሁሉ በቂ ምክንያቶች አይደሉም ። ወደ ከተማ ጎዳና ውጣ ። ድሆችንና ጒንድሾችን እንካሶችንና ዕውሮችንም ወደዚህ አግባ ።

አገልጋዩም ይህን ሁሉ አድርጎ ተመለሰና ፡— ጌታ ሆይ ፣ እንዳዘዝሽኝ ተደርጎአል ። ነገር ግን ገና ስፍራ አለ አለው ። ጌታውም አገልጋዩን ፡— ቤቴ እንዲሞላ ወደ መንገድና ወደ ቅጥር ውጣና ይገቡ ዘንድ ግድ በላቸው ። እላችኋለሁና ፣ ከታደሙት ከእነዚያ ሰዎች አንድ ስንኳ እራቴን አይቀምስም አለው ።

ስለዚህ አገል.ጋዮቹ ቤቱን በድሆች በጒንድሾች በእንካሶችና በዕውሮች ሞሉት ። እነርሱ በጣም ተደስተው ነበር ። የቤቱም ጌታ ደግሞ በጣም ተደስቶ ነበር ።

(ሉቃ. ፲፬ ፣ ፯—፳፬ ተመልከት ።)



## ፲፯

## ዳግመኛ መወለድ ።

ኒቆዲሞስ የሚባል አንድ የአይሁድ አለቃ ነበረ ። ይህም ሰው በሌሊት ወደ ኢየሱስ መጥቶ ፦ መምህር ሆይ ፣ መምህር ሆነህ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደ መጣህ እናውቃለን ። እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ከሆነ በቀር አንተ የምታደርጋቸውን እነዚህን ምልክቶች ሊያደርግ የሚችል የለም አለው ። ኢየሱስም መልሶ ፦

እውነት እውነት እልሃለሁ ፣ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር ፣ የእግዚአ ብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም አለው ። ኒቆዲሞስም ፦

ሰው ከሸመገለ በኋላ ፣ እንዴት ሊወለድ ይችላል ? ሁለተኛ ወደ እናቱ ማኅፀን ገብቶ ይወለድ ዘንድ ይችላልን ? አለው ። ኢየሱስም መለሰ ። እንዲህ ሲል ፦

እውነት እውነት እልሃለሁ ፣ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ፣ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም ። ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው ፣ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው ።

ኢየሱስ ይህን ሲል ሥጋ ከሥጋ ዳግመኛ መወለድ አለበት ማለቱ አይደለም ። ሥጋና ደም ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገቡ አይችሉም ማለቱ ነው ።

ኒቆዲሞስና ኢየሱስ ሲነጋገሩ ፣ በውጭ ነፋስ ሲነፍስ ድምፁን ይሰሙ ነበር ። ኢየሱስም ፦ ዳግመኛ ልትወለዱ ያስፈልጋችኋል ስላልሁህ አታድ ንቅ ። ነፋስ ወደሚወደው ይነፍሳል ፣ ድምፁንም ትሰማለህ ። ነገር ግን ከወ ዴት እንደ መጣ ወዴትም እንዲሄድ አታውቅም ። ከመንፈስ የተወለደ ሁሉ እንዲህ ነው አለው ።

ኒቆዲሞስም መልሶ ፦ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል ? አለው ።

ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው ፡— አንተ የእስራኤል መምህር ስት ሆን ፡ ይህን አታውቅምን ? እውነት እውነት እልሃለሁ ፡ የምናውቀውን እን ናገራለን ያየነውንም እንመሰክራለን ፡ ምስክራችንንም አትቀበሉም ። ስለ ምድራዊ ነገር በነገርኋችሁ ጊዜ ካላመናችሁ ፡ ስለ ሰማያዊ ነገር ብነግራችሁ እንዴት ታምናላችሁ ? ከሰማይም ከወረደው በቀር ወደ ሰማይ የወጣ ማንም የለም ፡ እርሱም በሰማይ የሚኖረው የሰው ልጅ ነው ።

በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይ ጠፋ የሰው ልጅ ይሰቀል ዘንድ ይገባዋል ።

በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይ ጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአ ልና ። ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ ፡ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም አልላከውምና ። በእርሱ በሚያምን አይፈረድበትም ፤ በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስላላመነ ፡ አሁን ተፈርዶበታል ። ብርሃንም ወደ ዓለም ስለ መጣ ፡ ሰዎችም ሥራቸው ክፉ ነበርና ከብርሃን ይልቅ ጨለ ማን ስለ ወደዱ ፡ ፍርዱ ይህ ነው ። ክፉ የሚያደርግ ሁሉ ብርሃንን ይጠላ ልና ፡ ሥራውም እንዳይገለጥ ወደ ብርሃን አይመጣም ፤ እውነትን የሚያ ደርግ ግን ሥራው በእግዚአብሔር ተደርጎ እንደ ሆነ ይገለጥ ዘንድ ወደ ብርሃን ይመጣል ።

(ዮሐ. ፫ ፡ ፲—፳፩ ተመልከት ።)

@et_christian_library

# ፲፱

## አሥር ቈነጃጅት በሰርግ ።



## ፲፱

# አሥር ቈነጃጅት በሰርግ ።



ኢየሱስ ለመጸለይ ወደ ደብረ ዘይት ብዙ ጊዜ ይሄድ ነበር ። ይህ ስፍራ ደብረ ዘይት የተባለበት ምክንያት ፡ ብዙ ወይራ ስለ ተተከለበት ነው ። ደብረ ዘይት የሚገኘው በኢየሩሳሌም አቅራቢያ ነው ።

አንድ ቀን ኢየሱስ በደብረ ዘይት ተቀምጦ ሳለ ፡ ደቀ መዛሙርቱ መጡና ፡—

ንገረን ፡ ይህ መቼ ይሆናል ? የመምጣትህና የዓለም መጨረሻ ምልክቱስ ምንድር ነው ? አሉት ።

ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው ፡— ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ ። ብዙዎች ፡— እኔ ክርስቶስ ነኝ እያሉ በስሜ ይመጣሉና ፤ ብዙዎችንም ያስታሉ ። በዚያን ጊዜ ማንም ፡— እነሆ ፡ ክርስቶስ ከዚህ አለ ወይም ፡— ከዚያ አለ ቢላችሁ አትመኑ ፤ ሐሰተኞች ክርስቶሶች ይነሣሉና ። ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ ይሞክራሉ ። እንግዲህ እንዳያስቱአችሁ ተጠንቀቁ ።

ስለዚህ እናንተ ደግሞ ተዘጋጅታችሁ ኑሩ፤ የሰው ልጅ በማታስቡበት ሰዓት ይመጣልና። ስለዚያች ቀንና ስለዚያች ሰዓት ግን ከአባት በቀር የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ ልጅም ቢሆን የሚያውቅ የለም።

ከዚህ በኋላ ኢየሱስ በደብረ ዘይት እንደ ተቀመጠ፤ ይህን ምሳሌ ተናገረ፤—

በዚያን ጊዜ መንግሥተ ሰማያት መብራታቸውን ይዘው ሙሽራውን ሊቀበሉ የወጡ አሥር ቈነጃጅትን ትመስላለች። ከእነርሱም አምስቱ ሰነፎች አምስቱም ልባሞች ነበሩ። ሰነፎቹ መብራታቸውን ይዘው ከእነርሱ ጋር ዘይት አልያዙምና፤ ልባሞቹ ግን ከመብራታቸው ጋር በማሰሮአቸው ዘይት ያዙ።

ሙሽራው ሳይመጣ ዘገየ። ቈነጃጅቱም፤— ሙሽራው ለምን ዘገየ? አሉ። ብዙ ጊዜም ስለ ዘገየ፤ ሁሉ እንቅልፍ እንቅልፍ አላቸውና ተኙ። እስከ እኩለ ሌሊት ድረስ ተኙ። እኩለ ሌሊትም ሲሆን፤— እነሆ፤ ሙሽራው ይመጣል፤ ትቀበሉት ዘንድ ውጡ የሚል ውካታ ተሰማ። ስለዚህ ቈነጃጅቱ ሁሉ ተነሥተው መብራታቸውን አዘጋጁ። ሰነፎቹ ልባሞቹን፤— ሙሽራው እስከ አሁን ዘገየ። እኩለ ሌሊት ነው፤ መብራታችንም ሊጠፋብን ነው። ስለዚህ ከዘይታችሁ ትንሽ ስጡን። እኛ በቂ ዘይት የለንምና መብራታችን ሊጠፋብን ነው። እናንተ በማሰሮአችሁ ውስጥ ዘይት አላችሁ አሉአቸው።

ልባሞቹ ግን መልሰው፤— ምናልባት ለእኛና ለእናንተ ባይበቃስ፤ ይልቅስ ወደሚሸጡት ሄዳችሁ ለራሳችሁ ግዙ አሉአቸው።

ስለዚህ ዘይት ወደሚሸጡት ሄደው ዘይት ገዙ። ነገር ግን ሺያጩ ተኝቶ ስለ ነበረ፤ ሲያስነሡት ዘገዩ።

እነርሱም ሊገዙ በሄዱ ጊዜ፤ ሙሽራው መጣ። ተዘጋጅተው የነበሩትም ከእርሱ ጋር ወደ ሰርግ ገቡ፤ ደጁም ተዘጋ። ሰነፎቹ ቈነጃጅት ዘይታቸውን ከገዙ በኋላ፤ ደግሞ መጡና፤— ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ፤ ክፈትልን አሉ። እርሱ ግን መልሶ፤— እውነት እላችኋለሁ፤ አላውቃችሁም። ወደ ሰርጉም መግባት አትችሉም አለ።

ስለዚህ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን፤— ቀኒቱንና ሰዓቲቱንም አታውቁምና እንግዲህ ንቁ። የሰው ልጅ በማታስቡበት ሰዓት ይመጣል አላቸው።

(ማቴ. ፳፬፤ ፫—፭፤ ፳፫፤ ፳፬፤ ፴፮፤ ፵፬፤ ፳፭፤ ፩—፲፫ ተመልከት።)





# ፳
# የመጨረሻው ፍርድ

ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ፡— የምመጣበትን ሰዓት አታውቁምና ተጠንቀቃችሁ ጠብቁ ካላቸው በኋላ ፥ በዓለም መጨረሻ ፍርድ እንደሚሆን ነገራቸው ። ነገሩን ግልጥ ለማድረግ ፈልጎ ፥ በግንና ፍየልን ሥዕላዊ መግለጫ በማድረግ እንዲህ ሲል ተናገረ ፡—

የሰው ልጅ በክብር በሚመጣበት ጊዜ ክእርሱም ጋር ቅዱሳን መላእክት ሁሉ ፥ በዚያን ጊዜ በክብሩ ዙፋን ይቀመጣል ። የዓለም ሕዝብ ሁሉ ለፍርድ በፊቱ ይሰበሰባሉ ። በዙፋኑም ተቀምጦ እረኛ በጎቹን ክፍየሎች እንደሚለይ ፥ የዓለምን ሕዝብ ሁሉ እርስ በርሳቸው ይለያያቸዋል ። በጎችን በቀኙ ፍየሎችንም በግራው ያቆማቸዋል። (ኢየሱሰ ይህን ሲል የአንድ አገር ሕዝብ በቀኙ የሌላውም በግራው ይቆማል ማለቱ አይደለም ። በእያንዳንዱ አገር የሚገኙት ሰዎች ሁሉ እርስ በርሳቸው አንድ በአንድ ይለያያሉ ማለቱ ነው ።)

ንጉሡም በቀኙ ያሉትን ጻድቃን እንዲህ ይላቸዋል ፡— እናንት የአባቱ ብሩካን ፥ ኑ ፤ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ ። ተርቤ አብልታችሁኛልና ፥ ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና ፥ እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛልና ፥ ታርዤ አልብሳችሁኛልና ፥ ታምሜ ጠይቃችሁኛልና፥ ታስሬ ወደ እኔ መጥታችኋልና ።

ጻድቃንም መልሰው ይሉታል ፡— ጌታ ሆይ ፥ ተርበህ አይተን መቼ አበላንህስ ? ወይስ ተጠምተህ አይተን መቼ አጠጣንህ ? እንግዳ ሆነህስ

አይተን መቼ ተቀበልንህ ? ወይስ ታርዘህ አይተን መቼ አለበስንህ ? ወይስ ታመህ ወይስ ታስረህ አይተን መቼ ወደ አንተ መጣን ?

ንጉሡም ጻድቃንን መልሶ ፦ እውነት እላችኋለሁ ፤ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ወንድሞቼ ወይም እህቶቼ ወይም ልጆቼ ለአንዱ እንኳ ስላደረጋችሁት ለእኔ እደረጋችሁት ። ከሁሉ ከሚያንሰው ለአንዱ ሰው ምግብ ከሰጣችሁ ወይም ለተጠማው ሰው ውኃ ካጠጣችሁ ወይም እንግዳ ከተቀበላችሁ ወይም የታረዘውን ካለበሳችሁ ወይም የታመሙትንና የታሠሩትን ከጠየቃችሁ ፤ ለእኔ አደረጋችሁት ይላቸዋል ።

በዚያን ጊዜ ንጉሡ በግራው ያሉትን የተረገሙትን ደግሞ ይላቸዋል ፦ እናንተ ርጉማን ፤ ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀ ወደ ዘላለም እሳት ከእኔ ሂዱ ። ተርቤ አላበላችሁኝምና ፤ ተጠምቼ አላጠጣችሁኝምና ፤ እንግዳ ሆኜ አልተቀበላችሁኝምና ፤ ታርዤ አላለበሳችሁኝምና ፤ ታምሜ ታስሬም አልጠየቃችሁኝምና ።

ርጉማኑም ደግሞ ይመልሱና ፦ ጌታ ሆይ ፤ ተርበህ ወይስ ተጠምተህ ወይስ እንግዳ ሆነህ ወይስ ታርዘህ ወይስ ታመህ ወይስ ታስረህ መቼ አይተን አላገለገልንህም? ይሉታል ። ያን ጊዜ ንጉሡ መልሶ ርጉማኑን ፦ እውነት እላችኋለሁ ፤ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ለአንዱ ስላላደረጋችሁት ፤ ለእኔ ደግሞ አላደረጋችሁትም ይላቸዋል ። ርጉማኑ ወደ ዘላለም ቅጣት ፤ ጻድቃን ግን ወደ ዘላለም ሕይወት ይሄዳሉ ።

(ማቴ. ፳፭ ፤ ፴፩—፵፮ ተመልከት ።)

# ፳፮

# ስለ ብፁዓን ።



@et_christian_library

## ፳፩

# ስለ ብፁዓን ።



እንድ ቀን ኢየሱስ ብዙ ሰዎች ባየ ጊዜ ፣ ወደ ተራራ ወጣ ። በተቀመጠም ጊዜ ፣ ደቀ መዛሙርቱ ወደ እርሱ ቀረቡ ። አፉንም ከፍቶ አስተማራቸው ። ያስተማረው ትምህርት የተራራ ስብከት ይባላል ። ትምህርቱን እንዲህ በማለት ጀመረ ፦—

በመንፈስ ድሆች የሆኑ ብፁዓን ናቸው ፣ መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና ።

የሚያዝኑ ብፁዓን ናቸው ፣ መጽናናትን ያገኛሉና ።

የዋሆች ብፁዓን ናቸው ፣ ምድርን ይወርሳሉና ።

ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው ፣ ይጠግባሉና ።

የሚምሩ ብፁዓን ናቸው ፣ ይማራሉና ።

ልበ ንጹሖች ብፁዓን ናቸው ፣ እግዚአብሔርን ያዩታልና ።

የሚያስተራርቁ ብፁዓን ናቸው ፣ የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና ።

ስለ ጽድቅ የሚሰደዱ ብፁዓን ናቸው ፣ መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና ።

እነዚህ ቃላት የእርሱ መንግሥት አባሎች የሚሆኑትን ይገልጣሉ ። እንግዲህ ኢየሱስ በእነዚህ ቃላት ያስተማረው ትምህርት ምን እንደ ሆነ በአጭሩ እንመልከት ።

በመንፈስ ድሆች የሆኑ ብፁዓን ናቸው፤ መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና ። በመንፈስ ድሆች የሆኑ ሲል ምን ማለቱ ነው ? በምድራዊ ንብረት ድሆች የሆኑ ማለቱ አይደለም ። ምክንያቱም፤ ድሀ ሰው በመንፈሱ ኵራተኛ ይሆን ይሆናል ። እንዲሁም ባለ ጠጋ ሰው ከመንግሥተ ሰማያት ውጭ ነው ማለቱ አይደለም ። ምክንያቱም፤ ባለ ጠጋ ሰው በመንፈስ የተዋረደ ይሆን ይሆናል ። በመንፈስ ድሆች የሚላቸው እግዚአብሔር ፊት ለመቅረብ የማይገባን ነን ብለው የሚያስቡትን ሁሉ ነው ። እንደነዚህ ያሉ ሰዎች ሁሉ በምድራዊም ሆነ በመንፈሳዊ በኩል የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ከእግዚአብሔር ብቻ ይጠባበቃሉ፤ መንግሥተ ሰማያትም ይገባሉ ።

የሚያዝኑ ብፁዓን ናቸው፤ መጽናናትን ያገኛሉና ። የሚያዝኑ ሲል ምን ማለቱ ነው ? ድሆች የሚለው ቃል በምድራዊ ድህነት የሚገኙትን ሁሉ እንደማይመለከት፤ እንዲሁም የሚያዝኑ የሚለውም ቃል የሚወዱት ሰስ ሞተባቸው የሚያዝኑትን ሁሉ አይመለከትም ። ዋናው ተፈላጊ የኃዘኑ ምክን ያት ነው ። ደግሞም ዋናው ተፈላጊ የሚያዝኑበት መንፈስ ነው ። ምድራዊ ነገር ስለ ጠፋባቸው የሚያዝኑ፤ መጽናናትን እንደሚያገኙ እርግጠኞች ሊሆኑ አይችሉም ። ስለ ኃጢአታቸው የሚያዝኑ እንዲሁም ስለ ዓለም ክፋት የሚያዝኑ ግን፤ ከእግዚአብሔር መጽናናትን እንደሚያገኙ እርግጠኞች ሊሆኑ ይችላሉ ።

ኢየሱስ የዋሆች ብፁዓን ናቸው፤ ምድርን ይወርሳሉና ሲል ምን ማለቱ ነው ? የዋሆች እነማን ናቸው ? የዋሆች ለራሳቸው ምንም ክብር የማይፈልጉ ናቸው ። እነርሱ የተዋረዱ ናቸው ። የተዋረዱም ስለ ሆኑ፤ ምንም ዓይነት ጭቅጭቅ ወይም ሁከት አይፈጥሩም ። በእግዚአብሔርም ይታመናሉ፤ እንደ ፈቃዱም ይኖራሉ ። እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች የእግዚአብሔርን ትምህርት ሊቀበሉ ይችላሉ ።

ኢየሱስ፤ ምድርን ይወርሳሉ የሚለው ለምንድር ነው ? ዝና ወይም የከበ ሬታ ስፍራ ለማግኘት የማይሞክሩትን ትሑታን፤ ዝምተኞችንና ትምህርቱን የሚቀበሉትን እግዚአብሔር ይወዳል ። መንግሥተ ሰማያትን የሚወርሱ እንደ እነርሱ ያሉት ናቸው ።

ኢየሱስ፡— ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው፤ ይጠግባሉና ሲል ምን ማለቱ ነው ?

ይጠግባሉ ። ምክንያቱም፤ እግዚአብሔር እነርሱ ጽድቅን እንዲያገኙ

ይወዳልና ። እንዲሁም ሰዎች ጽድቅን ሲራቡና ሲጠሙ ይደሰታል ። ስለዚህ ያጠግባቸዋል ። ኃጢአት ግን ማንንም አያጠግብም ።

የሚምሩ ብፁዓን ናቸው ፤ ይማራሉና ። እነዚህ ቃላት ምን ያስረዱናል?

እንደሚታወቀው አብዛኛውን ጊዜ የሚምሩ ይማራሉ ፤ የማይምሩም ምንም ምሕረት አያገኙም ። ወንድማቸውን የሚምሩ ለራሳቸው ደግሞ ምሕ ረት ያገኛሉ ። እግዚአብሔር መሐሪ ስለ ሆነ ፤ ጻድቅም ሌሎችን ይምራል ። መሐሪ ስለ ሆነም ፤ ከእግዚአብሔር ምሕረት ያገኛል ።

ኢየሱስ ፦ ልበ ንጹሖች ብፁዓን ናቸው ፤ እግዚአብሔርን ያዩታልና ባለ ጊዜ ፤ ምን ማለቱ ነው ።

ልበ ንጹሕ ማለት ልበ መልካም ማለት ነው ። ደግሞ ንጹሕ ማለት ክፉ አሳብ የሌለበት የጸዳ ማለት ነው ። ንጹሕ መሆን ማለት መልካምና ክፉ ያልተደባለቀበት ማለት ነው ። እግዚአብሔር ንጹሕ ነውና ንጹሕ ያል ሆኑ እርሱን አያዩትም ።

ኢየሱስ ፦ የሚያስተራርቁ ብፁዓን ናቸው ፤ የእግዚአብሔር ልጆች ይባላ ሉና ሲል ምን ማለቱ ነው ? ሰላም የሚወዱ ብፁዓን ናቸው እንዳላለ እናስተ ውል ። ምክንያቱም ፤ ሁሉም ሰላም የሚወዱ ናቸው ። ስለ ሰላምም የሚናገሩ ብዙዎች አሉ ። ሰላምን የሚያደርጉ ግን ጥቂቶች ናቸው ። እነርሱም የእግዚ አብሔር ልጆች ናቸው ።

ኢየሱስ ፦ ስለ ጽድቅ የሚሰደዱ ብፁዓን ናቸው ፤ መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና ባለ ጊዜ ፤ ምን ማለቱ ነበረ ?

መሰደድ ማለት ሰዎች ስለ ጽድቅ ያሠቃዩሃል ማለት ነው ። ኢየሱስ ፦ መልካም ስላደረጋችሁ ከተሰደዳችሁ ፤ መንግሥተ ሰማያትን ትወርሳላችሁ ይለናል ።

በተሰደድን ጊዜ ፤ ይህን ጥቅስ ማስታወስና እየደጋገምን መንገር ታላቅ መጽናናት ነው ። ነገር ግን ስደታችን እውነትን በመከተል ምክንያት ወይም ስለ ክርስቶስ እንዲሆን እርግጠኞች መሆን አለብን ። ክፉ ፤ ሠርተን ወይም የራሳችንን መንገድ በመከተል ብንሰደድ ፤ ንስሐ ከልገባን በስተቀር ፤ ለመባ ረክ ተስፋ ማድረግ የለብንም ።

(ማቴ. ፩ ፤ ፫—፲ ተመልከት ።)

## ፭፪

## በፍጥነት ታረቁ ።

ኢየሱስ ለሁላችን በእውነት ከባድ መስሎ የሚታየንን አንድ ነገር እንድናደርግ ይነግረናል ። ይህም ጠላቶቻችንን መውደድ ነው ። ኢየሱስ ከወንድማችን ጋር መጣላት ወይም በወንድማችን መቈጣት እንኳ እንደ ማይገባን ይነግረናል ። ለእኛም ይህ በጣም ከባድ ይመስላል ። እንዲያውም እንዲህ ብሎአል ፦

ለቀደሙት ፦ አትግደል እንደ ተባለ ሰምታችኋል ፤ የገደለም ሁሉ ፍርድ ይገባዋል ። እኔ ግን እላችኋለሁ ፤ በወንድሙ ላይ የሚቈጣ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል ።

ኢየሱስ በዚህ ላይ በታላቁ የፍርድ ቀን ስለሚሆነው የሚናገር ይመስላ ል ። መጣላት ከፍቅር ሕግ ውጭ ስለ ሆነ ፤ የእግዚአብሔርን ፍርድ ያመጣል። በጎች ከፍየሎች ስለሚለዩበት የፍርድ ቀን አንብበናል ። በዚያን ቀን ሌሎችን የማይወዱ ፍርድ ይቀበላሉ ።

ኢየሱስ ትምህርቱን እንዲህ ሲል ቀጠለ ፦

ወንድሙንም ደንቆሮ የሚለው ሁሉ የገሃነመ እሳት ፍርድ ይገባዋል ።

ደንቆሮ በሚለው ሰው ላይ የተወሰነው ፍርድ ከባድ ይመስላል ። ይህ እንደገና የሚያመለክተው በፍርድ ቀን ፍርድ እንደሚገባን ነው ። ገሃነመ እሳት ፤ በጎች ከፍየሎች ስለሚለዩበት ቀን ባነበብነው ታሪክ ውስጥ እንዳለው ዓይነት ነው ። በዚያ ታሪክ ዓመፀኞች የዘላለም እሳት ይፈረድባቸዋል ተብሎ አል ። በዚያ ምዕራፍ ላይ ያ የዘላለም እሳት ገሃነመ እሳት ባይባልም ፤ ገሃ ነመ እሳት ነው ። ጥል የገሃነመ እሳት ነገር እንጂ የመንግሥተ ሰማያት ነገር አይደለም ።

እስቲ ቀጥሎ ያለውን የኢየሱስ ቃል እናንብ ፦

እንግዲህ መባህን በመሠዊያው ላይ ብታቀርብ ፤ በዚያም ወንድምህ አንዳች በአንተ ላይ እንዳለው ብታስብ ፤ በዚያ በመሠዊያው ፊት መባህን ትተህ ሂድ ። አስቀድመህም ከወንድምህ ጋር ታረቅ ። በኋላም መጥተህ መባህን አቅርብ ።

ኢየሱስ ፤ እኛ ከአንድ ሰው ጋር እንኳ ከተጣላን ፤ ለእግዚአብሔር የምና ቀርበው መባችን ዋጋ አለው ብለን መጠባበቅ እንደማንችል ይነግረናል ።

ኢየሱስ ለእግዚአሔብር መባችንን ከማቅረባችን በፊት ፥ መታረቅ እንዳለ ብን ይነግረናል ። እርግጥ ነው ! ይህን ማድረግ እጅግ በጣም ከባድ ነው ።

ኢየሱስ ቀጥሎ እንዲህ አለ ፦ — አብረኸው በመንገድ ሳለህ ከባላጋራህ ጋር ፈጥነህ ተስማማ ፤ ባላጋራህ ለዳኛ እንዳይሰጥህ ዳኛም ለሎሌው ፥ ወደ ወኅኒ ቤትም ትጣላለህ ፤ እውነት እልሃለሁ ፥ የመጨረሻዋን ሳንቲም እስክት ከፍል ድረስ ከቶ ከዚያ እትወጣም ።

ይህም ማለት ፥ ብንጣላ ፥ ከሳሻችን ነገሩን ፍርድ ቤት ከማድረሱ በፊት ፥ እርቅን መሻት አለብን ። ከሳሻችን ፍርድ ቤት ቢወስደን ፥ ተፈርዶብን ወደ ወኅኒ ቤት እንገባ ይሆናል ማለት ነው ።

እንግዲህ ብንቈጣ ወይም ሰውን ብናስቈጣ ፥ በተቻለን ፍጥነት መታ ረቅ ይገባናል ። ከባላጋራችን ጋር ወደ ዳኛ ፊት ከመቅረባችን በፊት ፥ ሁል ጊዜ በፍጥነት እንታረቅ ።

(ማቴ. ፭ ፥ ፳፫—፳፮ ተመልከት ።)



@et_christian_library

## ፭፫

# ጠላቶቻችሁን ውደዱ ።

እሁን ልንፈጽመው እጅግ በጣም ወደሚያስቸግረው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ደርሰናል ። ኢየሱስ ጠላቶቻችሁን መውደድ አለባችሁ ይለናል ። ከዚህም የከበደ የለም ። ጠላቶቻችንን እንጠላለን ፥ እንወጋለን ፥ እንገድላለንም። ማንኛውም መንግሥት ቢሆን ፥ ኢየሱስ የተናገረውን ለማድረግ አልተነሣም። እጅግ ከባድ መስሎ ታይቶአል ። ይህ ነገር ለአብዛኛዎቹ ሰዎች ከባድ ብቻ ሳይሆን ፥ ሞኝነትም ይመስላቸዋል ። ምክንያቱም ፥ ኢየሱስን ፥— ጌታ ሆይ ፥ ጌታ ሆይ ፥ እንለዋለን ፤ ነገር ግን እንድናደርገው ያዘዘንን አላደረግንም ። ስንጣላና ጦርነት ስናደርግም ፥ ያዘዘንን የሚቃወም ነገር እናደርጋለን ።

እርሱ ያስተማረን የሚከተሉት ናቸው ፥—

ዓይን ስለ ዓይን ጥርስም ስለ ጥርስ እንደ ተባለ ሰምታችኋል ። እኔ ግን እላችኋለሁ ፥ ክፉውን አትቃወሙ ፤ ዳሩ ግን ቀኝ ጉንጭህን በጥፊ ለሚመታህ ሁሉ ሁለተኛውን ደግሞ አዙርለት ፤ እንዲከስህም ሸሚዝህን እንዲወስድ ለሚወድ ኮትህን ደግሞ ተውለት ፤ ማንም ሰው እንድ ምዕራፍ ትሄድ ዘንድ ቢያስገድድህ ፥ ሁለተኛውን ከእርሱ ጋር ሂድ ።

ይህም ማለት በጭራሽ አትቈጣ ፥ ለሰው ሁሉ በጎ ፈቃድ ይኑርህ ማለት ነው ። ከዚህም በበለጠ የበደለኸውን ሰው እንደምትወድና ልትረዳ እንደምትፈቅድ አሳይ ። ስለዚህ ሸሚዝህን ቢወስድ ፥ በፍቅርና በደስታ ኮትህን ደግሞ ተውለት ። አንድ ኪሎ ሜትር ከእርሱ ጋር እንድትሄድ ቢያስገድድህ ፥ ሁለት ወይም ሦስት ኪሎ ሜትር ከእርሱ ጋር ሂድ ። ይህን ስታደርግ ግን ፥ እንዳትቈጣ ። ይህንም ስታደርግ ፥ ሥጋህ ደስ ባይለው እንኳ ፥ መንፈስህ ደስ ይለዋል ።

ዓይን ስለ ዓይን ጥርስም ስለ ጥርስ ማለት አንድ ሰው ጥርስህን ቢሰብር ፥ አንተም ጥርሱን ትሰብረዋለህ ማለት ነው ። እንዲሁም አንድ ሰው ዓይንህን ቢያጠፋ ፥ አንተም ዓይኑን ታጠፋዋለህ ማለት ነው ። ኢየሱስ ግን ፥— ክፉውን አትቃወሙ ። ክፉን በክፉ አትመልሱ ፤ አትጣሉ ። አትበቀሉ ፥ በቀል የእግዚአብሔር ነውና ብሎ አስተማረን ።

ቀኝ ጉንጭህን በጥፊ ለሚመታህ ሁለተኛውን ደግሞ አዙርለት ። ነገር ግን ሁለተኛውን ጉንጭህን ስታዞር ፥ እንድትወደውና እንድትደሰት አስተውል ። ሲመታህ ብትናደድ ግን ፥ የዚህን የከባድ ትምህርት መንፈስ ተላልፈሃል ።

እዚህ ላይ ፡— አንድ ሰው ሲመታኝ ፣ ላለመናደድ አልችልም ትል ይሆናል ። ይህ እውነት ነው ። ይህ በዓለም እጅግ በጣም ከባድ ነገር ነው ። ነገር ግን ኢየሱስ ሊፈጽመው ቻለ ። አንዳንድ ትዕግሥተኞችም ሊፈጽሙት ይችላሉ ። ራስህንም ከቍጣ ነጻ አድርገህ መጠበቅ አስፈላጊ ነው ።

ኢየሱስ ከባዱን ትምህርት እንዲህ ሲል ቀጠለ ፡— ባልንጀራህን ውደድ ጠላትህንም ጥላ እንደ ተባለ ሰምታችኋል ። እኔ ግን እላችኋለሁ ፤ በሰማያት ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ ፤ የሚረግሙአችሁንም መርቁ ፤ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ ፤ ስለሚያሳድዱአችሁም ጸልዩ ፤ እርሱ በክፉዎችና በበጎዎች ላይ ፀሐይን ያወጣልና ፤ በጻድቃንና በኃጢአተኞችም ላይ ዝናብን ያዘንባልና ። የሚወዱአችሁን ብትወዱ ፤ ምን ዋጋ አላችሁ ? ወንድሞቻችሁንም ብቻ እጅ ብትነሡ ፤ ምን ብልጫ ታደርጋላችሁ ? እንግዲህ የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደ ሆነ እናንተ ፍጹማን ሁኑ ።

ጥልንና ጦርነትን ከእኛ ብናርቅ ፤ በእውነት ፍጹማን እንሆናለን ። ግን ጥልንና ጦርነትን ከእኛ ልናርቅ እንችላለን ? ጠላቶቻችን ባንቃወማቸው ፤ ምን ያደርጉብናል ? ነጻ ልንሆን እንችላለን ? ኢየሱስ ይህን ሁሉ አደረገ ። ቢገድሉትም እንኳ ፤ ነጻ ነበረ ።

(ማቴ. ፭ ፡ ፴፰—፵፰ ተመልከት ።)

@et_christian_library



## ፳፬

## የጌታችን ጸሎት ።



## ፳፬

## የጌታችን ጸሎት ።

በማቴዎስ ወንጌል በምዕራፍ ፭ ፥ ፮ ና ፯ የሚገኘውን የተራራ ስብከት እንብበን ነበር ። ይህ ስብከት በዓለም ከሚገኙት ከታወቁት ስብከቶች ሁሉ እጅግ በጣም ትልቁ ነው ። የሃይማኖት ሊቃውንት የተራራውን ስብከት ከስብከት ሁሉ እጅግ ትልቁ ነው ይሉታል ። የሰው ጆሮ ያልሰማውን ታላቅ እውነት ያስተምራል ይላሉ ። ነገር ግን ጥቂቶች ሰዎች ብቻ ይከተሉታል ። በዚህ ስብከት ውስጥ የሚገኘው እውነት በጣም ከፍተኛ ነው ፤ ነገር ግን አብዛኞቹ ሰዎች ሊደረግ የማይቻል ትምህርት ነው ይላሉ ። ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ መድኃኒታችን ስንቀበልና ከእርሱ ብቻ እርዳታ ስንፈልግ ፥ እርሱ እንዳስተማረን ልንኖር እንችላለን ። ደግሞ ይህን ትምህርት ያስተማረን ታላቁ መምህር ኢየሱስ ፥ ይህን አስገራሚ የሕይወት መንገድ እንድንከተል መድኃኒታችንና ረዳታችን ሊሆን ይፈልጋል ።

በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ ፮ ኢየሱስ ለድሆች እንዴት እንደምንሰጥና ወደ እግዚአብሔር እንዴት እንደምንጸልይ እንዲህ ሲል ያስተምረናል ፡—

ለሰዎች ትታዩ ዘንድ ምጽዋታችሁን በፊታቸው እንዳታደርጉ ተጠንቀቁ ፤ ለድሆች በስውር ስጡአቸው ። ግብዞች ምጽዋት ሲያደርጉ ፥ በሰው ዘንድ ሊከበሩ እንዲታዩ ያደርጋሉ ። እነርሱ የሚቀበሉት ዋጋ የሰው ምስጋና ነው። ግን እግዚአብሔር አያመሰግናቸውም ። አንተ ግን ምጽዋት ስታደርግ ፥ ቀኝህ የምትሠራውን ግራህ አትወቅ ። ለድሆች በስውር ስጣቸው ። በስውር የሚያይህ አባትህም በግልጥ ይከፍልሃል ፥ ያመሰግንሃልም ።

ስትጸልዩም እንደ ግብዞች አትሁኑ ፤ ለሰው ይታዩና ይመስገኑ ዘንድ በመንገድ ማዕዘን ወይም በጸሎት ቤት ቆመው መጸለይን ይወዳሉና ። የሚቀበሉት ዋጋ የሰው ክብር ብቻ ነው ። ነገር ግን ከእግዚአብሔር ምንም ዋጋና ክብር አይቀበሉም ፤ ምክንያቱም ፥ ግብዞች በመሆናቸው ይጠላቸዋል ።

አንተ ግን ስትጸልይ ፥ ወደ እልፍኝህ ግባ ። መዝጊያህንም ዘግተህ በስ ውር ላለው አባትህ ጸልይ ፤ በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ይከፍልሃል ። ብዙ ሰዎች በመናገራቸው ብዛት እንዲሰሙ ይመስላቸዋል ። እናንተ ግን ስት ጸልዩ ፥ እንደ እነርሱ በከንቱ አትድገሙ ። ስለዚህ አትምሰሉአቸው ፤ ሳትለም ኑት አባታችሁ የሚያስፈልጋችሁን ያውቃልና ። እንግዲህ እናንተስ እንዲህ ብላችሁ ጸልዩ ፦

በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ ፥

ስምህ ይቀደስ ፤

መንግሥትህ ትምጣ ፤

ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን ፤

የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን ፤

እኛም ደግሞ የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን ፤

ከክፉም አድነን እንጂ ወደ ፈተና አታግባን ፤

መንግሥት ያንተ ናትና ኃይልም ክብርም ለዘላለሙ ፤

አሜን ።

ለሰዎች ኃጢአታቸውን ይቅር ብትሉ ፥ የሰማዩ አባታችሁ እናንተን ደግሞ ይቅር ይላችኋልና ፤ ለሰዎች ግን ኃጢአታቸውን ይቅር ባትሉ ፥ የሰማዩ አባታችሁ ኃጢአታችሁን ይቅር አይላችሁም ።

የጌታችንን ጸሎት በዓለም ያሉት ክርስቲያኖች አብዛኛውን ጊዜ የሚጠ ቀሙበት ነው ። እንደምታውቀውና ሁልጊዜም እንደ ተጠቀምህበት እያጠራ ጥርም ። የጌታችንንም ጸሎት በምንጸልይበት ጊዜ ፥ ስለ እያንዳንዱ ቃል ማሰብ ይኖርብናል ።

(ማቴ. ፮ ፥ ፮—፲፭ ተመልከት ።)



፳፫

አስቀድማችሁ
የእግዚአብሔርን
መንግሥት ፈልጉ ።

@et_christian_library

በዚህ በመጨረሻው ምዕራፍ ከተራራው ስብከት እንደገና እናነባለን ። ኢየሱስ እንዲህ አለ ፤—

ብልና ዝገት በሚያጠፉት ሌቦችም ቈፍረው በሚሠርቁት ዘንድ ለእናንተ በምድር ላይ መዝገብ አትሰብስቡ ፤ ነገር ግን ብልም ዝገትም በማያጠፉት ሌቦችም ቈፍረው በማይሠርቁት ዘንድ ለእናንተ በሰማይ መዝገብ ሰብስቡ ፤ መዝገብህ ባለበት ልብህ ደግሞ በዚያ ይሆናልና ።

ለኢየሱስ የምንመልሰው መልሳችን ፦ ለምን በምድርም በሰማይም መዝገብ አይሰበሰብም ? ሀብታም ሰው ድሀ ሰው ከሚያደርገው ይበልጥ መልካም ነገር ሊያደርግ ይችላል ? የሚል ይሆን ይሆናል ።

ኢየሱስ ለዚህም መልሱን ሰጥቶአል ፦ ለሁለት ጌቶች መገዛት የሚቻለው ማንም የለም ፤ ወይም አንዱን ይጠላል ሁለተኛውንም ይወዳል ፤ ወይም ወደ አንዱ ይጠጋል ሁለተኛውንም ይንቃል ፤ ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ መገዛት አትችሉም ።

ኢየሱስ በእነዚህ ቃላት እማካይነት ለሁለት ጌቶች መገዛት ብንሞከር ለሁለቱም በሚገባ ለመገዛት አለመቻላችንን ያስረዳናል ።

ደግሞም ኢየሱስ እንዲህ አለ ፦ ስለዚህ እላችኋለሁ ፥ ስለ ነፍሳችሁ በምትበሉትና በምትጠጡት ፥ ወይም ስለ ሰውነታችሁ በምትለብሱት አትጨነቁ ፤ ነፍስ ከመብል ሰውነትም ከልብስ አይበልጥምን ?

እንግዲህ ፦ ምን እንበላለን ? ምንስ እንጠጣለን? ምንስ እንለብሳለን ? ብላችሁ አትጨነቁ ፤ ይህ ሁሉ እንዲያስፈልጋችሁ የሰማዩ አባታችሁ



@et_christian_library

ያውቃልና ። ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም
ፈልጉ ፥ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል ።

ዕድሜ ልካቸውን ሀብት ለማግኘት የሚፈልጉ ብዙዎች ሰዎች ይህን
የኢየሱስን ትምህርት ይንቃሉ ። ኢየሱስን ያከብሩ ይሆናል ። ሆኖም ፥ ካስ
ተማራቸው ትምህርቶች አንዳንድ ትምህርቶችን ይጠላሉ ። ኢየሱስ ግን ፦
ልባም ሰው ሕይወቱን ሙሉ ብልና ዝገት በሚያጠፉት ሌቦችም ቈፍረው
በሚሠርቁት ዘንድ ለእርሱ በምድር ላይ መዝገብ አይሰበስብም ይላል ።

ሰታሪኝ ሳስ ፥ የዚህ ምድር መዝገብ እንዴት በቶሎ እንደሚጠፋ ታያ
ለህ ። ሰዎች መዝገባቸውን በደንብ ለመጠበቅ ይሞክራሉ ፤ ግን በተቻላቸው
መጠን ቢጠብቁትም እንኳ ፥ አንድ ቀን ይወሰድ ይሆናል ። በተጨማሪም ፥
ሞት የማይቀር ግዴታ ነው ። በዚያን ጊዜም ገንዘባችንን ወይም ሀብታችንን
ከእኛ ጋር ልንወስድ አንችልም ። ከዚህም የባሰው ፤ በፍርድ ዙፋን ፊት ስን
ቀርብ ፦ አንተ ሞኝ ፥ በዓለም ካሉት ሰዎች አብዛኞቹ እንደ ተራቡ ፥ እንደ
ተጠሙ ፥ እንደ ታረዙና እንደ ታመሙ እያወቅህ እነዚህን ከመርዳት
ይልቅ መዝገብ ሰበሰብህ ። በምድር ያሉትን ችግረኞችን ካልረዳህ ፥ በምድር
ያለው መዝገብህ በሰማይ ይኰንንሃል የሚል ቃል እንሰማለን ። የችግረ
ኞችን እቤቱታ ብትንቅ ፤ በሰማይ መዝገብ አይኖርህም ። እግዚአብሔ
ርም በፍርድ ቀን ይንቅሃል ።

ነገር ግን መዝገብ ለራሳችሁ በሰማይ ብትሰበስቡ ፥ ያ መዝገብ የዘላ
ለም ነው ። ብል ወይም ዝገት እያጠፋውም ፥ ሌቦችም ቈፍረው እይሠርቁትም።

ኢየሱስ ፦ ብልም ዝገትም በማያጠፉት ሌቦችም ቈፍረው በማይሠር
ቁት ዘንድ ለእናንተ በሰማይ መዝገብ ሰብስቡ እያለ በልዩ ልዩ መንገድ
የሚነግረን ስለዚህ ነው ።

ስለዚህ ኢየሱስ ፦ በዚህ ዓለም ስላለው ንብረታችሁ አትጨነቁ ። ስለ
ምትበሉት አትጨነቁ ። ስለምትለብሱት አትጨነቁ ። ስለ ማንኛውም ነገር
በፍጹም አትጨነቁ ። በአባታችሁ ልትታመኑ ትችላላችሁና ። የሚያስፈልጋ
ችሁን ያውቃል ይሰጣችኋልም ። ስለዚህ ለነገ አትጨነቁ ፤ ነገ ለራሱ ይጨ
ነቃልና ። በመጨነቅ ነገን ከዛሬ የተሻለ ለማድረግ አትችሉም ። እግዚአብ
ሔር ሊረዳችሁ ነገ እዚያ ይገኛል ። ስለዚህ በቂ እምነት ቢኖራችሁ ፥ ለነገ
አትጨነቁም ። ለቀኑ ክፋቱ ይበቃዋል ይላል ።

(ማቴ. ፮ ፥ ፲፱—፴፬ ተመልከት ።)